Centre for Information Resilience

# በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች

ዘ ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሪዚሊየንስ

እ.ኤ.አ 2024

# 1. አጠቃላይ ሀሳብ

የሰዎች ግላዊና ማህበራዊ ህይወት በኢንተርኔት እና በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንፀባረቀ መምጣቱ፣ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል በሚደረገው አንቅስቃሴ ላይ አዲስ ፈተና ይዞ ብቅ ብሏል። ኢንተርኔት መረጃን ለማሰራጨት፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር፣ ለአክቲቪዝም እና ለፖለቲካዊ ቅስቀሳዎች የማገልገሉን ያህል በ  የታገዘ ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃትና መገለል አመቺ መድረክ ሲሆን ይስተዋላል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላከል በኢንተርኔት ላይ የሴቶችን ደህንነት ለመጠበቅና ሴቶች በሁሉም ማህበረሰባዊ መስተጋብሮች ላይ ንቁ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያግዛል።

ዘ ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሪዚሊያንስ (ሲ.አይ.አር ) በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዘላቂ ተጽዕኖ ለመረዳት  ከዚህ በፊት የተፃፉ ፅሁፎችን በማጣቀስ እና በሚዲያ፣ በሲቪል ማህበረሰብ እና በሌሎች ህዝባዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ 14 ሴቶችን ስለ ግል ልምዳቸው ቃለ መጠይቅ አድርጓል። ይህ ጥናት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መልክ (አይነትና መጠን)፣ የሚፈፀሙበትን ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ፣ አላማ እና የሚፈጥሩትን ተፅዕኖ ያሳያል። ሲ.አይ.አር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶች ከፍተኛ የሆነ ፆታን መሰረት ያደረጉና ሴትነትን የሚያሳንሱ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች እንደሚደርስባቸው መረዳት ችሏል። ሲ.አይ.አር ይህ ጥናት በማህበረሰቡ ዘንድ መነጋገሪያ ርዕስ በመሆን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ውጤታማና በመረጃ በተደገፈ መልኩ ለመከላከል የሚያደርገውን ጥረት ያግዛል ብሎ ያምናል።

## ቁልፍ ግኝቶች

የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት በኢንተርኔት ላይ ያለው የሴቶች ጥቃት፤ ሴቶች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ብሔር ተኮር ጉዳዮች ላይ ባላቸው አስተዋፅኦ ዙሪያ ያለውን የተዛባ ማህበረሰባዊ አመለካከት ያንፀባርቃል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በጣም ከመስፋፋቱ የተነሳ የተለመደ እና ትኩረት የተነፈገው ጉዳይ መሆኑን በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉ ሴቶች በሙሉ ድምፅ ተስማምተዋል። በዚህ ችግር ምክንያት ብዙዎቹ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በነፃነት ከመግለፅ ይልቅ ዝምታን የመረጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ኢንተርኔትን መጠቀም እስከማቆምና ማህበራዊ መስተጋብራቸውን እስከመገደብ እንደደረሱ ገልፀዋል ።

ሲ.አይ.አር ኢትዮጵያ ውስጥ ባካሄደው ጥናት መሰረት ወንዶችና ሴቶች ላይ የሚደርሱት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በይዘት፣ በአላማና በመጠን የጎላ ልዩነት አላቸው። ቃለ መጠይቅ በተደረገላቸው ሴቶች መሰረት ወንዶች በፖለቲካ አቋማቸው፣ እይታቸውና በአመለካከታቸው ጥቃት ሲደርስባቸው ሴቶች ደግሞ በመልካቸውና ማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ሚና ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል። ለምሳሌ ታዋቂ ሴቶች በፀጉራቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በሰውነታቸው ክብደት፣ በትዳር፣ በፍቅር ህይወታቸው እና ባላቸው የልጆች ብዛት በማህበራዊ ትስስር ድረ-ገጾች መነጋገሪያ ሲሆኑ ይህ አካሄድ ተመሳሳይ ቦታ ላይ ባሉ ወንዶች ላይ እንደማይስተዋል የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ሴቶች ላይ ያነጣጠሩ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ሴቶች ስለ ፖለቲካ ለማውራት ብቁ እንዳልሆኑ፣ የጓዳ ስራ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ወይም ስለመብቶቻቸው

መጠየቃቸው ከኢትዮጵያ መርህ ጋር እንደማይሄድ አድርገው የሚስሉ መሆናቸውን የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡፡

የጥቃት አይነቶቹም ስድቦች፣ ዛቻዎች፣ ማስፈራሪያዎችና የስም ማጥፋትና ማጠልሸት ተግባሮች ሲሆኑ ብዙ ሴቶች የአስገድዶ መድፈር፣ የሞት እና የመታሰር ማስፈራሪያዎች ደርሰባቸዋል፡፡ ስለ ሴቶች መብት መጠየቅ/መሟገት የግብረሰዶማዊነት ፍረጃ እንደሚያስከትል የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች አንስተዋል፡፡ ግብረሰዶማዊነት እንደ ስድብ ከመታየቱም በላይ ህገ-ወጥ እንደመሆኑ ይህ ስም የተሰጣቸው ሴቶች በህግ ሊጠየቁና ሊታሰሩ ይችላሉ።

እንደ ቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች እምነት የጥቃቶቹ ፈፃሚዎች ዓላማ ሴቶችን ማዋረድ፣ ማስፈራራትና ሀሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልፁ ማድረግ ነው ። በተጨማሪም የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የስነልቦና ጉዳት ከማምጣት፣ የስራና የቤተሰብ ህይወት ላይ ጫና ከማድርግ አልፎ ሴቶች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዳይገልጹና ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ዝምታን እንዲመርጡ ማድርጉን የውይይቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሴቶች ውስጥ 78 ከመቶ የሚሆኑት ስለደረሰባቸው የኢንትርኔት ላይ ጥቃት ሲያወሩ ፍርሃትና ጭንቀት እንደሚሰማቸው አክለው ገልጸዋል፡፡

ቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሴቶች የትኛውንም ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ሲጠቀሙ ደህንነት እንደማይሰማቸው ገልፀዋል። ፌስቡክ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚፈፀምበት ዋነኛው ማህበራዊ ሚዲያ ቢሆንም ኤክስ (በቀድሞ ስሙ ትዊተር) ፣ ቲክቶክ፣ ዩቱዩብ እና ኢንስታግራም ላይም ተመሳሳይ ጥቃቶች አሉ። ጥቃቶቹም በተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገጾች ላይ መፈፀማቸው ከማህበራዊ ትስስር ድህረገጾቹ ድክመት ይልቅ ችግሩ ማህበረሰባዊ መሆኑን ያሳያል ።

ብዙ ሴቶች የደረሰባቸውን አካላዊ ጉዳትና እስር ያስታውሳሉ። አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ መታሰሯን ስትገልፅ ሌላ ተሳታፊ እስር ለማምለጥ ሀገር ጥላ እንደተሰደደች ተናግራለች። ሲ.አይ.አር የአካላዊ ጉዳቶቹና የእስሮቹ መንስኤ በቀጥታ ከኢንተርኔት ጥቃት ጋር የተያያዘ ወይም ኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ ያለው ችግር የአንድ ጥቃት ሁለት መገለጫዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ አልቻለም። አንዳንድ ጊዜ በኢንተርኔት እና በእውነተኛው ዓለም ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች መሀል ያለው ግንኙነት ግልፅ ነው። ለምሳሌ በኢንተርኔት ላይ የሚደርሱ የእስር ማስፈራሪያዎች በእውነተኛው ዓለም ላይ የስነልቦና ጠባሳ ከመፍጠራቸውም አልፎ ሴቶች በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ስጋት ያሳድርባቸዋል፡፡

ይህን ችግር በማያዳግም መንገድ ለመቅረፍ የሚቀረጹት እስትራቴጂዎች የችግሩን ስር መሰረት መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ካነሷቸው መፍትሄዎች መካከል ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረጉ የተዛቡ አመለካከቶችንና አድሎዎችን ማስቀረት እንዲሁም ኢንተርኔት ላይ የሚገኙና ከኢንተርኔት ውጪ ባሉ ዋና ሚዲያዎች ላይ የሴቶችን ተሳትፎ መጨመር ይገኙበታል ።

## ቀጣይ ጥናት

ሲ.አይ.አር ይህን ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ ተከታታይ ውይይቶችና አውደ ጥናቶችን በማካሄድ ፆታን መሰረት ባደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ዙሪያ ቁጥራዊ ጥናት አካሂዷል። ይህ ጥናት በጥልቀት ያተኮረው በኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ የሚደገፉ ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ላይ ሲሆን፤ በሶስት የማህበራዊ ድህረ-ገጾች ላይ የተጋሩ ይዘቶችን መርምሯል፡፡ ውጤቶቹም ከዚህኛው ጥናት ጋር በአንድ ላይ ይፋ ይሆናል።

**ማሳሰቢያ:** ይህ ጥናት አስጨናቂና ሊረብሹ የሚችሉ ምስሎችን አጠቃቀም ለመቀነስ ቢሞክርም ኢንተርኔት ላይ ጥቃት ጋር የተያያዙና ለአንድ አንባቢዎች አስጨናቂ ሊሆኑ የሚችሉ ይዘቶች አሉት።

## 2. ማውጫ


*1. አጠቃላይ ሀሳብ* ..... 1

**ቀጣይ ጥናት** ..... 2

*2. ማውጫ* ..... 4

*3. መግቢያ* ..... 5

**3.1 የጥናቱ ዓላማ** ..... 6

**3.2 የጥናቱ ወሰን** ..... 6

*4. የጥናቱ ዘዴ* ..... 8

**4.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች** ..... 9

**4.2 አውደ ፅሁፋዊ ትንተናና የተዛማጅ ፅሁፎች ምልከታ** ..... 9

*5. ትንታኔ* ..... 11

**5.1 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች መልክ** ..... 11

5.1.1 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች መነሻ የሚሆኑ አመለካከቶች ..... 11

5.1.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች ..... 19

5.1.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ ድግግሞሽና መጠን ..... 21

**5.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የሚፈፀሙባቸው መድረኮች** ..... 22

5.2.1 የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች አጠቃቀም ..... 22

5.2.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረተ ያደረጉ ጥቃቶች የሚፈፀሙባቸው መድረኮች ..... 23

5.2.3 ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ውጪ ባሉ ሌሎች ዋና ሚዲያዎች ላይ ይታያል? ..... 25

**5.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዓላማ** ..... 26

5.3.2 የጥቃት ፈፃሚዎቹ ማንነት ..... 27

5.3.3 የጥቃቶቹ ቅንጅት ..... 28

**5.4 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተፅዕኖ** ..... 29

5.4.1 በግል፣ በስራ እና በቤተሰብ ህይዎት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ..... 29

5.4.3 የሴቶች ድምፅ መታፈን ..... 30

5.4.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች መለመድ ..... 31

5.4.4 ከኢንትርኔት ውጪ ያሉ ጥቃቶችና እስራቶች ..... 32

**5.5 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል የተቀመጡ ምክሮችና መፍትሄ ሀሳቦች** ..... 33

*6. መደምደሚያ* ..... 36

# 3. መግቢያ

ማህበራዊ ሚዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና አድሎዎች እንዲስፋፉ መንገድ ከፍቷል ። ማህበራዊ ሚዲያ እንደ መረጃ ምንጭነት፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንደ መገናኛና በመንግስት ከተያዙ ሚዲያዎች ውጪ ሀሳቦች በነፃነት ለማንሸራሸሪያነት እንደ አማራጭነት ሊያገለግል ይችላል ።[1] በዚህም ምክንያት ማህበራዊ ሚዲያ በፖለቲካ ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶችን በማበረታታት ዴሞክራሲያዊና ያልተማከለ በማድረግ[2] ለአክቲቪዝም ሆነ ለተለያዩ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች መሰረት ሆኗል።[3] ነገር ግን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃትና መድሎ መድረክ እየሆነ ይገኛል። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ማህበረሰቡ ስለፆታ እና ፆታ ነክ ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከት በመቅረፅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።[4] በዚህም ተጽዕኖ ፈጣሪነቱ ምክንያት ፆታዊ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።[5] በቴክኖሎጂ የተደገፈ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከስነልቦናዊ ጉዳትና የመናገር ነጻነትን እና የሰብዓዊ መብቶችን ከመወሰን አልፎም በእውነተኛው አለም ላይ ለጥቃት መጋለጥ የመሳሰሉ ጥልቅ ተፅዕኖዎች አሉት። ይህ ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ በጉዳዩ ላይ የተሰሩ ጥናቶች እጥረት አለ።

ማህበራዊ ሚዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ የወንዶች የበላይነት የሚንፀባረቅበት መድረክ ነው። በጥናት መሰረት ከአጠቃላይ ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ሴቶች 34.1 በመቶ ብቻ ይሸፍናሉ።[6] በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የኢንተርኔት ተደራሽነት ልዩነት ምክንያት የተጠቀሰው አማካይ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ መጠን፣ አካባቢ እና የቋንቋ ልዩነቶችን ያገናዘበ አይደለም ። ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት አንፃር ሲወዳደር በኢትዮጵያ ያለው የኢንተርኔት ተደራሽነት አነስተኛ ቢሆንም የተለያዩ የዜና አውታሮችና ፣የንግድ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በኢንተርኔት ላይ እንቅስቃሴ ያረጋሉ ። በተለያዩ ሚዲያዎችና ሲቪል ማህበራት ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር በሚደረግባት ኢትዮጵያ፣ ማህበራዊ ሚዲያ አንደ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ሆኖ በማገልገል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።.

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸው ሴቶች የሚደርስባቸውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የዳሰሰ ሲሆን ይህም የተካሄደው በከፊል በታዋቀረ (Semi-structured) ቃለ መጠይቅ ነው። እንደውጤቱም በኢንተርኔት ላይ የሚደርሱ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ማህበረሰቡ፣ ሴቶች በብሔር ፣ በፖለቲካ እና በሃይማኖት ዙሪያ ስላላቸው ሚና ያለውን የተሳሳተ አመለካከትን ያሳያል። በኢንተርኔት ላይ

---

[1] Workneh (2019) African Journalism Studies, Available at:
https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/23743670.2020.1729832

[2] Skjerdal and Gebru (2020) Media Culture & Society, Available at:
https://www.researchgate.net/publication/340832244_Not_quite_an_echo_chamber_ethnic_debate_on_Ethiopian_Facebook_pages_during_times_of_unrest; De Zúñiga, Molyneux, and Zheng (2014) Journal of Communication, Available at: https://academic.oup.com/joc/article-abstract/64/4/612/4086027?redirectedFrom=fulltext&login=false; Holt et al (2013) European Journal of Communication, Available at: https://journals.sagepub.com/doi/abs/10.1177/0267323112465369'; Valenzuela (2013) American Behavioral Scientist, Available at: https://journals.sagepub.com/doi/10.1177/0002764213479375

[3] Yilma (21 September 2021) Cambridge University Press, Available at: https://www.cambridge.org/core/journals/journal-of-african-law/article/abs/on-disinformation-elections-and-ethiopian-law/AD43AE2160E071FEF73EE8E4128F0B7A

[4] Mannila (2017) Available at: http://norden.diva-portal.org/smash/get/diva2:1092200/FULLTEXT01.pdf

[5] Kassa and Sarikakis (2022) Feminist Media Studies, Available at:
https://www.tandfonline.com/doi/epdf/10.1080/14680777.2021.1917640

[6] Ibid.

ያለው ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ትንኮሳ የስነልቦና ቀውስ፣ ከስራ የመሰናከል እና ከኢንተርኔት ውጪ ባለው ዓለም ሀሳብን መግለፅ አለመቻል የመሳሰሉ የእውነተኛ ዓለም ጉዳቶች አምጥቷል ።

## 3.1 የጥናቱ ዓላማ

በዚህ ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰሩ ሴት ጋዜጠኞች፣ አክቲቪስቶች፣ የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ጋር በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዙሪያ ጥልቅና በከፊል የተዋቀረ (semi structured) ቃለ መጠይቅ ከተደረገ በኃላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል ።

**1 የጥቃቶቹ መልክ (አይነትና መጠን)** - የጥቃት አይነቶቹ ምንድን ናቸው? በጥቃት አድራሾቹ የሚፀባረቁ ልዩ ትርክቶች አሉ ወይ? ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በኢትዮጵያ ውሰጥ ምን ያህል የተንሰራፋ ነው?

**2. የጥቃቶቹ መድረክ -** ጥቃቶቹ በየትኛው ማህበራዊ ትስስር ድህረ ገጽ ላይ ይደርሳሉ? ችግሩ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ልዩነት አለው? ጥቃቶቹ በአደባባይ መድረኮች (በትዊቶች፣ ይፋ የፌስቡክ ልጥፎች፣ ወዘተ) ውይስ በቀትታ የመልዕክት አማራጮች (ዋትስአፕ፣ ሜሴንጀር እና ቴሌግራም) ነው የሚዘነዘሩት?

**3. ዓላማ -** ትንኮሳ አድራሾቹ ምን ለማሳካት ታሳቢ አድርገው ነው ጥቃቶቹን የሚሰነዝሩት? ጥቃቶቹስ የተቀናጁ ናቸው?

**4. ተፅዕኖ-** እነዚህ ጥቃቶች ኢላማ በተደረጉ ግለሰቦች ሙያ፣ የግል ህይወት እና ቤተሰቦች ላይ የሚያደርሱት ተጽዕኖዎች ምን ይመስላሉ? በእለት-ተእለት ኑሯቸው እና በስራዎቻቸው ላይ የሚደርጓቸው እንቅስቃሴያቸው ላይ ጫና ፈጥረዋል?

ይህ ጥናት ማህበራዊ ሚና ያላቸው ሴቶች ላይ የሚደርሰው በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚደርስበትን መድረክና በጉዳዩ ያሉ ትርክቶችን በመረዳት ሰፊ ለሆነው ቁጥራዊ ጥናት ግብአት እንዲሆን ታስቦ የተሰራ ነው።[7]

## 3.2 የጥናቱ ወሰን

ሲ.አይ.አር በሚዲያ፣ በሲቪል ማህበረሰብ እና ሌሎችም ማህበራዊ ሚና ባላቸው ሴቶች ላይ የሚደርሰውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመዳሰስ ከ ከመጋቢት- ሚያዚያ 2023 እ.ኤ.አ ቃለ መጠይቆች ሲያደርግ ቆይቷል። በእነዚህ ቃለ መጠይቆች ወቅት ስለ ጥቃቶቹ መልክ/ይዘት፣ መጠን ፣ ተፅዕኖና የሚፈፀሙበት የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ አይነት ለመረዳት ተችሏል። የፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተጎጂዎች በማነጋገር የችግሩን ስፋት እና በኢትዮጵያ ያሉ የሴቶች እና ልጃገረዶች የህይወት ተሞክሮ በጥልቀት ለመረዳት አስችሏል። እነዚህ ቃለ መጠይቆች ለቀጣዩ ቁጥራዊ ጥናት አውድ ለመስጠትና ለማጎልበት ይጠቅማሉ።

[7] ለበለጠ መረጃ በቁጥራዊ ጥናቱ ላይ የሚገኘውን የ2ኛ ዙር ጥናት ዘዴና የስራ አካሄድ ክፍል ይመልከቱ

ይህ ጥናት በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገጾች መድረኮች ላይ ስለሚፈፀመው ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መረጃ እንዲኖራቸው ለተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች ሊጋራ ይችላል። በተጨማሪም ይህንን ችግር ለመከላከልና ለመቅረፍ ለሚደረጉ የተለያዩ ዘመቻዎች ላይ እንደ ግብአት ሊውሰድ ይችላል ።

# 4. የጥናቱ ዘዴ

ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸውና በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከደረሰባቸው 14 ሴቶች ጋር ጥልቅ ቃለ መጠይቆች አድርጓል ። የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ጋዜጠኞች፣ የህግ ባለሙያዎች፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያሉ መረጃዎችን እውነተኛነት የሚያረጋግጡ ባለሙያዎች (fact checkers) ነበሩ። በተጨማሪም በቃለ መጠይቁ ወቅት ሁሉም ተሳታፊ ሀሳቡን እንዲያጋራ እና ውይይቱ የሀገሪቷን ባህልና አኗኗር ዘይቤን ያማከለ ለማድረግ ልምድ ያላት አንድ ኢትዮጵያዊት የጥናት ባለሙያ ሲ.አይ.አር አካቷል።

ቃለ መጠይቆቹ በተቻለ መጠን አስተማማኝ እና ጥንቃቄ በሞላው መንግድ ለማድረግ  የሲ.አይ.አር ቡድን አባላት ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ዙሪያ ያጠነጠነ የኢንተርኔት ስልጠና ወስደዋል ። በዳርት ሴንተር (DART Center) በተዘጋጀው መርህና የሙራድ መርሆችን (Murad Code) በመመስረት ቃለመጠይቁ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያሟላ ተደርጓል ።

- በመረጃ የተደገፈ ፍቃድ- ሁሉም ተሳታፊዎች ከቃለ መጠይቁ በፊት የጥናቱን ዓላማ የሚገልፅ መረጃ ተሰጥቷቸው ፍቃዳቸውን በፅሁፍ እንዲያረጋግጡ ተደርጓል ።
- ከቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ፍቃድ ውጪ የተሳታፊዎች ማንነት ያልተገለፀ ሲሆን ማንኛውም ማንነታቸውን የሚገልፅ መረጃ ከቃለ-መጠይቁ ሪፖርትና ከመጨረሻው የጥናቱ ግለባጭ ላይ ተወግዷል። በተጨማሪም ከቃለ መጠይቁ በፊት ሁሉም ተሳታፊዎች ማንነታቸውን የሚገልፅ መረጃዎች በቃለ መጠይቁ ወቅት ከመጋራት እንዲቆጠቡ ተመክረዋል ።
- በተቻለ መጠን የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎችን ስሜት ፣ ፍላጎትና ጊዜ አጠቃቀም ለማክበር ተሞክሯል ።
- ደህንነት- በቃለ መጠይቁ ወቅት የተገኙ መረጃዎች ማለትም የቃለ መጠይቁ ፅሁፎች፣ ትርጉሞች እና ተሳታፊዎች ፍቃድ የሰጡባቸው ሰነዶች በጥናቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለሙያዎች ብቻ ሊያገኙት በሚችሉበት ኢግናይት (Egnyte) [8] በተባለ የመረጃ ቋት (folder) ውስጥ ተቀምጧል ።

ቃለ መጠይቆቹ በሴት ኢትዮጵያዊ የጥናት ባለሙያዎች በአማርኛ ቋንቋ የተካሄዱ ሲሆን ይህም የተከናወነው ፊት ለፊት በመገናኘት ወይም ዋትስአፕ እና ሲግናል በተባሉ የኢንተርኔት መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ነው። የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች በከፊል የተዋቀሩ (semi structured) ሲሆኑ ይህም ተሳታፊዎች በፈለጉት ጥያቄ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ ነጻነት ሰጥቷል። ጠያቂዎችም የሲ.አይ.አርን የስነ-ምግባር መርህ በተከተለ መልኩ በተሳታፊዎች ምላሽ ላይ ተመርኩዘው ተጨማሪ ጥያቄዎችን የመጠየቅ ነጻነት ተሰጥቷቸዋል። ሁሉም የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎችና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች በዚህ ጥናት ላይ በአማርኛና በእንግሊዘኛ አባሪ ተደርገው ተያይዘው ቀርበዋል ።

ከዚህም በመቀጠል የቃለ መጠይቁ ውጤት ተፅፎና ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ ለቀጣይ ትንተና ብቁ ተደርጓል። ትንተናውም እንግሊዘኛና አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ አባላትን ባካተተ የጥናት ቡድን የተሰራ ሲሆን ባለሙያዎቹ ከቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ልምድ ውስጥ ለጥናቱ ዓላማ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን ለመረዳት ሞክረዋል። እነዚህንም ነጥቦች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መልክ፣ የሚካሄዱባቸው የማህበራዊ ሚዲያ

[8] ሲ አይ አር ለስራዎቹ የሚጠቀምበት ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት ላይ የስራ ቦታ

አይነቶች፣ የጥቃቶቹ አላማ እና ተፅዕኖዎቹ ናቸው። እነዚህ ውጤቶች በቀጣይ በሚሰራው ቁጥራዊ ጥናት ላይ በሰፊው ይዳስሳሉ ።

ትንተናው አማርኛ እና እንግሊዘኛ ተናጋሪ በሆኑ ባለሙያዎች በጋራ መሰራቱ የተለያዩ የቋንቋና የባህል አንድምታዎች እንዳይጠፉ አድርጓል። የቃለ መጠይቁ ትንተና ውጤት የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ይሆናል።

## 4.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸው 14 ሴቶች ሲሆኑ እነዚህ ሴቶች በኢንተርኔት መድረኮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ያላቸው ወይም የነበራቸው ናቸው ። የታሳታፊዎች ቡድን ጋዜጠኞችን ፣ አክቲቪስቶችን ፣ የህግ ባለሙያዎችን ፣ የሰብዓዊ መብት መርማሪዎችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎችን እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን ያካተተ ሲሆን እነዚህ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትም የደረሰባቸው ናቸው ።

የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች የተመረጡት በኢትዮጵያ የጥናት ዘርፍ ውስጥ ከ10 ዓመት በላይ የጥናት ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ነው ። እንደ መነሻ 70 የሚሆኑ ሴቶች ቢመረጡም የጥናት ባለሙያዎች ማናገር የቻሉት 26ቱን ብቻ ነበር ። የተሳታፊዎች ትክክለኛ አድራሻ አለማግኘት ወይም ተሳታፊዎች ለቀረበላቸው ግብዣ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ አለመስጠት ለዚህ ችግር እንደ መንስኤነት ይቀመጣል ።

13 የሚሆኑ ሴቶች ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ሳይሰማሙ ቀርተዋል ወይም ጥናቱ ከተጀመረ በኃላ ለቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አቁመዋል። ብዙ ሴቶች ማንነታቸው በጥናቱ ላይ እንደማይገለፅ ማረጋገጫ ቢሰጣቸውም ቀርበው ልምዳቸውን ማጋራት አልፈለጉም። ሌሎች ቁጥራቸው በዛ ያሉ ሴቶች ደግሞ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት "የስራው አካል" ስለሆነ ስለ ጉዳዩ መነጋገር ጥቅም አለው ብለው እንደማያስቡ አጋረተዋል። ይህ ግኝት በራሱ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምን ያህል የተለመደ እንደሆነና እንደ ችግር እንደማይታይ ማሳያ ነው። የተሳታፊዎች ቁጥር በማነሱ ምክንያት የዚህ ጥናት ውጤት ችግሩን አሳንሶ ሊያቀርብ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 4.2 አውደ ፅሁፋዊ ትንተናና የተዛማጅ ፅሁፎች ምልከታ

ሲ.አይ.አር ዋናውን ጥናት ከማድረጉ በፊት አውደ ፅሁፋዊ ትንተናና የተዛማጅ ፅሁፎች ምልክታ አድርጓል። ሲ.አይ.አር አውደ ፅሁፋዊ ትንተናን ማድረጉ በሚዲያ፣ በሲቪል እና በህጋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ከመጨመሩም ጎን ለጎን እነዚህ ሁኔታዎች በሴቶች ኢንተርኔት አጠቃቀም ነጻነትና ኢንተርኔት ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመረዳት አስችሎታል። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶችም ይህንን ሀሳብ አጠናክረዋል ።

ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ ዉስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን በመመልከትና በእነዚህ ጥናቶች ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለመመልከት በማሰብ ጥልቅ የሆነ የተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ አድርጓል ። በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም አብዛኛዎቹ ጥናቶች ትኩረታቸዉ እንደ አጠቃላይ በአለም ላይና በምዕራባውያን ሀገራት ላይ ስላለው ሁኔታ ነው። አብዛኞቹ በዚህ የፅሁፍ ዳሰሳ ውስጥ የተካተቱት ፅሁፎች በእንግሊዘኛ ከተፃፉ ምንጮች ላይ የተገኙ ቢሆንም አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ የቡድን አባላቶቻችን

በአማርኛ ከተፃፉ ምንጮች ላይ የተገኙ ፅሁፎችን አጋርተውናል። በኢትዮጵያ ውስጥ በጉዳዩ ላይ ያሉት ጥናቶች ቁጥር ማነስ ይሄንን ጥናት ለማጥናት ተጨማሪ ማነቃቂያና ማበረታቻ ሆኗል።

ከተሰሩ ጥናቶችና ፅሁፎች እጥረት አንፃር የተዘማጅ ፅሁፎች ምልከታው ጠቅለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቷል። በመጀመሪያ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በትክክል ለመተርጎም ያሉትን መሰናክሎች ይቃኛል። በመቀጠልም ኢንተርኔት ላይ በተለይም በሴቶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች ይዳስሳል። በተጨማሪም ኢንተርኔት ላይ በሚደርሱ ጥቃቶችና በእውነተኛ ህይወት ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች መሃል ያለውን ግንኙነት ቃኝቷል። የተዘመጅ ፅሁፍ ዳሰሳው 7.1 ላይ በሙሉ ተያይዟል።

## 5. ትንታኔ

ጥናቱ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚዲያ፣ ሲቪል ማህበረሰብ፣ ትምህርት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ጉልህ ሚና ያላቸው ሴቶች ላይ የሚደርሰውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነት፣ ዓላማ፣ ተፅዕኖና ጥቃቱ የሚደርስበትን የማህበራዊ ትስስር ድህረ ገጽ መርምሯል። በከፊል የተዋቀረው ቃለመጠየቅ 14ቱ ሴቶች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን እውነተኛ የህይወት ልምድ ለመረዳትም አስችሏል።

በኢንተርኔት ላይ ያለው ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ፆታዊ ጥቃት ማህበረሰቡ፣ ሴቶች በፖለቲካ፣ በብሔርና በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሚና በማሳነስ ማንፀባረቂያ መሆኑን ጥናቱ ተመልክቷል። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በቴክኖሎጂ  የታገዘ ፆታዊ ጥቃት ሰለባ እንደሆኑ ባያጠራጥርም የጥቃቶቹ አይነት፣ ዓላማና ተፅዕኖ ግን በሁለቱ ፆታዎች መሃል የተለያየ እንደሆነ ጥናቱ ጠቁሟል።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የተስፋፋ ሲሆን በአደባባይም ሆነ በቀትታ የመልዕክት አማራጮች ላይ ይታያል። ጥቃቶቹ ታቅደውና ተቀነባብረው እንደሚፈፀሙ ማስረጃ ባይኖርም ሴቶችን ዝም ለማሰኘትና ከሌሎች የመሰሰሉ አላማዎች ተነስተው እንደሚፈፀሙ ጥናቱ ተረድቷል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ዛቻ በእውነተኛ ዓለም አኗኗር ላይም ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥሯል። የስነ-ልቦናዊ ጉዳት፣ የስራ ህይወት መስተጓጎል፣ ሴቶች ሀሳባቸው ከመግለፅ መቆጠብ፣ አካላዊ ጥቃትን እስራቶች ከእውነተኛ አለም ተፅዕኖዎች ውስጥ ይመደባሉ።

ይህ ትንተና የችግሩ ስፋትና መጠን በጥልቀት ያሳያል። በዚህ ትንተና ውስጥ የተካተቱት ሀሳቦች በቃለ-መጠየቅ ተሳታፊዎቹ ህይወት ላይ ያጠነጠኑና ተሳታፊዎቹ እንደተናገሩት በቀጥታ የተፃፈ ነው። ሲ.አይ.አር በተሳታፊዎቹ የተነሱ ውንጀላዎችን አላረጋገጠም ።


### 5.1 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች መልክ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ማህበራዊ ሚና ያላቸው ሴቶች ላይ የሚደርሰውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት መልክ (አይነትና ስፋት) መርምሯል። ይህም የጥቃቶቹን አይነት፣ ጥቃቶቹን የሚያነሳሱ አመለካከቶችን፣ የጥቃቶቹን ድግግሞሽና ስፋት ያካተተ ነው። ወንዶች ከብሔር፣ ከፖለቲካ ወይም ከሃይማኖት ጋር በተገናኙ ጉዳዎች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ሲደርስባቸው ለሴቶች ጥቃት መንስኤ የሆኑት ጉዳዮች ግን ለወንዶች ከተጠቀሱት ጉዳዮች የተለዩ ናቸው። የወንዶችን የበላይነት የሚያንፀባርቁ አመለካከቶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት አድርገው ለሚፈፀሙ ጥቃቶች ተጨማሪ መንገድ በመክፈት ሴቶች በእውነተኛ አለም ላይ የሚደርስባቸውን ችግር እያጎላ መጥቷል ።

#### **5.1.1 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች መነሻ የሚሆኑ አመለካከቶች**

በቃለ መጠይቆቹ ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲፈፀሙ የተለያዩ አመለካከቶችና ትርክቶች መነሻ እንደሚሆኑ ተጠቅሷል። ለምሳሌ ሴትን ዝቅ አርገው የሚያሳዩ አመለካከቶች (መልክ ላይ በማተኮር፣ ወሲባዊ ለሆኑ ጉዳዮች ብቻ እንደተፈጠሩ አድርጎ በማሰብ፣ በማህበረሰብና በቤት ውስጥ ያላቸውን

ሚና ዝቅ አድርጎ በማየት ዙሪያ ያሉ የጅምላ ፍረጃ/አመለካከቶች)፣ ብሔር፣ ፖለቲካና ግጭቶች፣ ሃይማኖትና የግብረሰዶም ውንጀላዎች ለጥቃቱ እንደመነሻ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሀሳቦች ያሳያሉ። ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በተናጠል ሊታዩ የሚችሉ ሳይሆኑ እርስ በእርስ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች እንደሆኑ መረዳት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ከብሔርና ሃይማኖት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከፖለቲካና ከግጭት ጋር ተያያዥ ለሆኑ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች እንደመነሻ ሊያገለግሉ ይችላሉ።እያንዳንዱ ምድብ እንደሚከተለው ይታያል።




*ምስል 1፡ በእያንዳንዱ ለጥቃቶች መነሻ በሚሆኑ አመለካከቶች ምክንያት ጥቃት የደረሰባቸውን የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች መጠን የሚያሳይ ግራፍ*

*በሚቀጥሉት ክፍሎች ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ ዝርዝር ይኖራል።*

### *5.1.1.1 የወንዶችን የበላይነት በማጉላት ሴቶችን የሚያሳንሱ አመለካከቶች*

በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሴቶች በሙሉ ኢንተርኔት ላይ ባሉ መድረኮች በሴትነታቸው ዝቅ ተደርገው እንደሚታዩ ገልፀዋል። ሴቶችና ወንዶች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም የጥቃቶቹ መልክ እንደሚለያዩ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በአንድ ድምፅ ተስማምተዋል። በተሳታፊዎቹ መሠረት ወንዶችም ሆነ ሴቶች ሃይማኖትና ብሔር-ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም ፆታን መሠረት ያደረጉ፣ በአካላዊ መልክ ላይ ያተኮሩና ማህበረሰብ ውስጥ ባላቸው ሚና ዙሪያ ግን ሴቶች ብቻ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ገልጸዋል።

በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ሴቶች በፀጉራቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በሰውነታቸው ክብደት፣ በትዳራቸው፣ በፍቅር ህይወታቸውና በልጆቻቸው መጠን መነጋገሪያ እንደሚሆኑና ይህ ተመሳሳይ ቦታ ላይ ባሉ ወንዶች ዙሪያ እንደማይስተዋል ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል። እንደተሳታፊዎቹ ገለፃ *"ወንዶች የግል ጥቃት አይደርስባቸውም። በመልካቸው፣ በትዳር ህይወታቸው እና በሌሎች የግል ህይወታቸው ጥቃት አይደርስባቸውም።"* አንድ ተሳታፊ ጋዜጠኛ እንደገለፀችው ወንዶች የሚደርስባቸው አስተያየት...

> *"ስላመነጬት ሀሳብ ሲሆን ሴቶች ግን በመልካቸውና በማህበራዊ ሚናቸው በዋነኝነት ጥቃት ይደርስባቸዋል። ሴቶችን የሚያሸማቅቁ ስድቦችና 'ልጆቿን አርፋ ታሳድግ፤ ቡና ብቻ ታፍላ እና ሴተኛ አዳሪ ብትሆን ይሻላታል' የሚሉ ንግግሮች አሉ"*

አንድ ጋዜጠኛ ይህንን ብላለች *“ወንዶች ወንድ ስለሆኑ ብቻ ጥቃት አይደርስባቸውም። የጥላቻ ንግግር በሁሉም ዘንድ የተንሰራፋ ቢሆንም ፆታቸውን በሚመለከት ግን ወንዶች አይጠየቁም። በአብዛኛው ካመነጩት ሀሳብ እና ካላቸው አመለካከት ጋር ተያያዥ ያላቸው አስተያየቶችን ነው የሚቀበሉት”* በተቃራኒ ሴቶች ግን ከተናገሩት ጉዳይ ጋር የማይገናኝ *“ልብሷ ን አይታችሁታል? ፣ ስለልብሷ ያላችሁን ሀሳብ በአስተያየት መስጫ ውስጥ አስቀምጡ”* የመሠሉ ሀሳቦች ይነሳባቸዋል። በአስተያየት መስጫ በታውም ላይ ስድቦችና የጥላቻ ንግግር ይከተላሉ። እንደነዚህ አይነት ጥቃቶች ለግል ጉዳይ ማህበራዊ ሚዲያን የሚጠቀሙም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ታዋቂ የሆኑ ሴቶች ላይ ይደርሳሉ። አንድ ጋዜጠኛ ስለ ሴቷ የአዲስ አበባ ከንቲባ ብትናገር ይህን ብላለች *“አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሆነ ነገር አጋራች። በመልዕክቱ ዙሪያ ከተሰጡ አስተያየቶች ውስጥ ከ70-80 በመቶ የሚሆኑት መልኳ ላይ ያተኮሩ ነበሩ”።*

አብዛኞቹ ሴቶች የደረሰባቸዉ ስድቦች ራሳቸዉን ለወሲብ ብቻ እንደተፈጠሩ አድርገዉ እንዲያስቡ አድርጓቸዋል። አንድ ጋዜጠኛ ፌስቡክ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሆነች ሴት ጋር ባደረገችዉ ቃለ መጠይቅ ከማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች *“ሴተኛ አዳሪ፣ ቅምጥ እና ሌሎች ፆታን መሠረት ያደረጉ ክብርን ዝቅ የሚያደርጉ ስድቦች”* እንደገጠማት ተናግራለች። በተመሳሳይ በቲክቶክ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነች ሴት ሹገር ዳዲዋ ማን እንደሆነ በተደጋጋሚ ስትጠየቅ ሌላ ጋዜጠኛ ደግሞ የሴተኛ አዳሪ ፍረጃዎች እንደሚደርሱባት ገልፃለች። ሌሎች ሁለት የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ደግሞ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ወሲባዊ ምስሎች በኢንተርኔት እንደሚለቀቅባቸዉ አልፎም ፊታቸዉ ወሲባዊ ከሆኑ ቪዲዮዎች ጋር በሀሰት ተቀናብሮ እንደሚሰራጭባቸው ተናግራለች።

ማህበረሰቡ ስለ ሴቶች ማህበራዊ ሚና ያለዉ የተሳሳተ አመለካከት ለአብዛኛው ጥቃት መነሻ እንደሆነ 50 በመቶ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያምናሉ። እነዚህም ሴቶች ስለፖለቲካ ለማዉራት ብቁ እንዳልሆኑ፣ የቤት ዉስጥ ስራ ብቻ መስራት እንዳለባቸዉ  ወይም ለመብታቸዉ መሟገታቸዉ ከኢትዮጵያ ባህልና እሴት ጋር እንደማይሄድ አርጎ ማሰብን ያካትታሉ። ለምሳሌ አንድ የዩቲዩቡ ፕሮግራም አዘጋጅ ይህን ብላለች *“አንድ የፕሮግራሜ ተከታታይ በብዙ ጉዳዮች ላይ እሺ የማለት ባህሪ ስላለሽ ጥሩ ሚስት ይወጣሻል በማለት አስታያየት ሰጥቷል። ይህም አስተያየት ሰጪው ሚስት ምን መምሰል እንዳለባት ስላለው አመለካከት ያሳያል”።* ሴቶች ካላቸው የሚስትነትና የእናትነት ሚና አንፃር ካላገቡ ለማሸማቀቅ መሞከር በኢንተነርኔት ዓለም ውስጥ ይታያል። በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ የኢንተርኔት ጦማሪ ይህን ብላለች *“እስካሁን ድረስ ስላላገባሁ ማሸማቀቂያ እና ስድቦች ይደርሱኛል። ‘አርጅተሻል ግን አላገባሽም’፣  ‘አንቺን ማንም ማግባት አይፈልግም’ የመሳሰሉ መልዕክቶች ይደርሱኛል ”*

የሴቶችን መብት ለማስከበር የሚደረግ እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያዊ ባህል መፍረስ ምክንያት እየሆነ ነው የሚለው ምክንያት ሴቶችን ዝቅ የሚያደርጉ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ መሠረት እንደሆነ አብዛኞቹ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። እንዲያውም እንደ አንድ አስታያየት ሰጪ ይህ ጉዳይ በፖለቲካዊ አመለካከት፣ በብሔርና ሃይማኖት ዙሪያ ልዩነት ላላቸው ሰዎች እንደ አንድነት መፍጠሪያ ሀኖ እያገለገለ ይገኛል።

> *“ በሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ልዩነቶች ምክንያት የማይስማሙ ሰዎች እንኳ ን የሴቶችን እንቅስቃሴ እና ከሴቶች መብት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመኮነን ይተባበራሉ። በኢ ንተርኔት ላይ እና  ከኢ ንተርኔት ውጪ ባለኝ ህይወት ብዙ ጥቃቶች ደርሶብኛል ። እነዚህ ጥቃቶችና ስድቦች በአጭር ጊዜ ውስጥ መሠራጨታቸው*

*ጥቃት አድራሾቹን ያበረታታል። የተገላጠ ልብስ አትልበሺ፣ ጡቶችሽን ሸፍኚና በስርዓት ተቀመጪ የሚሉ አስተያየቶች ደርሰውኛል። በአለባበሴም ምክንያት የማህበረሰቡን ህግ እየጣስኩ እንደሆነ ተነግሮኝ ያውቃል"*

አንድ የቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምዕራባዊያንን ትወኪያለሽ በሚል ተደጋጋሚ ውንጀላ እንደሚቀርብባት ተናግራለች። በራሷ አንደበት...

*"...የምዕራቢያውያንን ባህል ልታመጣብን ነው ይሉኛል። ባል ለቤተሰቡ ምግብ ማብሰሉንና የልጆቹን ዳይፐር መቀየሩን በመጥፎ ያዩታል ...የምዕራብያውያንን ባህል አምጥታቹ የኢትዮጵያን አኗኗር ዘይቤ ልታበላሹብን ነው ይላሉ"*

አንድ የግንኙነት ባለሙያ ደግሞ ገንዘብ ተከፍሏት የምዕራብያውያንን አኗኗር ዘይቤ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት እየሰራች ነው በሚል ተወንጅላለች፡

*" አንዳንድ ሰዎች ለአንድ ጉዳይ ድምፅ ለመሆን ግዴታ ገንዘብ ያስፈልጋል ብለው ማሰባቸው አይዋጥልኝም። ነገሮችን ሳደርግ የነበረው ተከፍሎኝ ሳይሆን ስለጉዳዩ ባለኝ ጥልቅ ስሜት ነው። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ድጋፍ የሚሰጡኝ ሰዎች በፆታ ጉዳዮች ላይ ባለኝ አቋም ካለመደገፍም አልፈው ቁጣና ስድብ ያደርሱብኛል። በህይወቴ ውስጥ የማደርጋቸው ማናቸውንም ነገሮች ከሴትነቴ ጋር ያገናኙታል። ለምሳሌ ለምን ከባለቤቴ ጋር እንዳልሆንኩኝ እና ለምን አንድ ልጅ ብቻ እንደወለድኩኝ የሚጠይቁና በምዕራብያዊያን የሴቶችን እንቅስቃሴ ለማስፋፋት ብር እንደተከፈለኝ አርገው የሚያስቡ ብዙ አሉ"*

በአብዛኛው ቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች መሰረት በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቅ ቦታ ባላቸው ሴቶች ላይ የሚሰነዘሩት ሴትን የሚያሳንሱ መልዕክቶች እንደ አጠቃላይ ህብረተሰቡ ስለ ሴቶች ያለውን አስተሳሰብ ማንፀባረቂያና ማሳያ ነው። ለምሳሌ አንድ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ *"ኢንተርኔት ላይ የምናየው ሁኔታ ከኢንተርኔት ውጪ ዓለም ላይ ያለው ኑሮ ቀጥተኛ ነፀብራቅ ነው። ይህን የእውነተኛ ዓለም ቀረብ ብለን ብንመለከት ደግሞ ምን ያህል በጥቃት የተሞላ እንደሆነ እንረዳለን"* በማለት ሀሳቧን አጋርታለች ።

ወንዶችም ሆነ ሴቶች ብሔራቸውን፣ የፖለቲካ አመለካከታቸውንና ሃይማኖታቸውን ተንተርሶ ጥቃት ቢደርስባቸውም የጥቃቱ መልክ/ይዘት ግን ሰፊ ልዩነት አለው። ከወንዶች ጋር ሲወዳደሩ ሴቶች ከተጠቀሱት ጉዳዮች በተጨማሪ ፆታን መሰረት አድርገው በማህበረሱ ከተሰጡ ሚናዎች ወጣ ሲሉ የሚደርሱባቸው ጥቃቶች አሉ።

ጥናቱ ሴቶች በኢንተርኔት ዓለም ላይ ያላቸው ተሳትፎ በጣም አናሳ እንደሆነና ከፍተኛ የሆነ ፆታን መሰረት ያደረገ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አሳይቷል። ስለሆነም የሴቶችን የኢንተርኔት ላይ ተሳትፎ ማሳደግና ሴቶችን የሚያገሉ ሀሳቦችን ለመሞገት የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ በኢንተርኔት ላይ የሚታዩትን ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል ውጤታማ መንገድ ነው።

### *5.1.1.2 ብሔር*

ግማሽ የሚሆኑት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ብሔርን እንደ አንድ ጥቃት ለመፈፀሚያ መነሻ አርገው አንስተውታል። እንደ ሴቶች ገለፃ በብሔር ወገንተኛነት፣ በአድሎአዊ ዘጋቢነት፣ የአንድ ብሔር የሚጧች ሰዎችን ቁጥር በማሳነስ፣ የውሸት መረጃዎች ለማሰራጨት ገንዘብ በመቀበል፣ ፅንፍ አዘል ሀሳቦች በማስተላለፍና የአንድ ብሔርን ክብር በማሳነስ ዙሪያ ውንጀላዎች ደርሰባቸዋል። አንድን ብሔር ለመጉዳት አሲራለች/አቅዳልች በሚል ከተሳታፊዎች

ውስጥ የአንዷ ተሳታፊ ፎቶግራፍ በኢንተርኔት ላይ ሲሰራጭ የሌላ ተሳታፊ ደግሞ የአንድ በብሔር የተዋቀረ ታጣቂ ቡድን አባል ነሽ በሚል የጥቃት ዒላማ ሆና እንደነበር ተናግራለች ።

በሴቶች መብት ዙሪያ በሚሰራ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ውስጥ የምትሰራ የማህበራዊ ሚዲያ አስተባባሪ ከአዛውንቶች ምርቃት ጋር በተገናኘ ባጋሩት የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገጽ ልጥፍ ላይ የደረሰባቸውን ፆታን መሰረት ያደረገ የኢንተርኔት ጥቃት እንዲህ በሚል አጋርታለች፡

*“ባጋራነው ልጥፍ ላይ ስለ ታላላቆቹ ሰዎች ብሔር የተናገርነው ነገር ባይኖርም አንዳንዶች ከሁለት ብሔር ብቻ የመጡ አባቶችና እናቶች ናቸው የተወከሉት በማለት ጀመሩ። በመቀጠልም ሌሎች ብሔሮች እናት የላቸውም ማለት ነው? በሴቶች ስም እርዳታ እየሰበሰባችሁ ነው! እንድትሞቱ ለፈጣሪ እንፀልያለን የሚሉ ሀሳቦች ተከትለው ነገሮች ተካረው ነበር።”*

በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሴት ጋዜጠኞችና የሰብዓዊ መብት መርማሪዎች በጦርነቶች ወቅት በሁለቱም የጦርነቱ ተሳታፊዎች በኩል ጥቃት እንደደረሰባቸው ገልጸዋል ። በቅርቡ በነበረው የሰሜኑ ጦርነት ወቅት ትዊተር ለእንደዚህ አይነት ጥቃቶች አመቺ መድረክ ሆኖ ነበር ። ትግሬዎችን ጨምሮ ሌሎች ብሔሮችም ላይ ያነጣጠሩ የዘር ማጥፋት አንደምታ የነበራቸው ፅሁፎች በሰፊው ሲጋሩ እንደነበር ሌሎች ጥናቶችም ዘግበዋል።[9] ትግሬዎች ፣ ደጋፊዎቻቸውና ዲያስፖራው ፣ትዊተርን ለአክቲቪዝም እና መረጃ ለመለዋወጫ አንደተጠቀሙበት ሲታሰብ የኢትዮጵያ መንግስትና ደጋፊዎቹ ማህበራዊ ሚዲያን *“የትግራይ አክቲቪስቶችን ለማጣጣል”* በዘመቻ ተጠቅመውበታል።[10] በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ የተሳተፉ አንድ ጋዜጠኛና አንድ የመረጃዎችን ትክክለኛነት የምታረጋግጥ ባለሙያ እንደገለፁት በትግራይ ጦርነት ጊዜ ለተለየ ብሔር ወግናችኋል በሚል በተደጋጋሚ ጥቃት ደርሶባቸዋል ።

*“የአንድ ብሔር አባል ነሽ በሚል ግምት አድሎዓዊ እና ከሀዲ የሚሉ ሰሞች ተሰጥተውናል። ጁንታና (በጦርነት ጊዜ የትግራይ ተወላጆችን ዝቅ ለማድረግ የተሰጠ ስም) ነፍጠኛ (አማራዎችን ዝቅ ለማድረግ በጥቅም ላይ የሚውል ስም) ተብያለው። እነዚህን ቃላቶች በሚዲያ ላይ ማለትም ሆነ መጠቀም አልፈልግም ”*

ሌላ ጋዜጠኛም ተመሳሳይ ውንጀላዎች ደርሰውባታል፡

*“ለምሳሌ በእናትሽ ‘ጁንታ’ ስለሆንሽ ሀገርሽን ትጠያለሽ ብለውኛል ። ይህ እውነት ባይሆንም ጥቃት አድራሾቹ ለሚፈልጉት ዓላማ ስላዋሉት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር ።”*

በሌላ በኩል አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ በብሔር ምክንያት የደረሰባት ጥቃት በፆታዋ ምክንያት ከደረሰባት የተለየ እንደሆነ ተናግራለች ።

---

- 9 DFR Lab (2021) Influential Ethiopian social media accounts stoke violence along ethnic lines, Medium, Available at: https://medium.com/dfrlab/influential-ethiopian-social-media-accounts-stoke-violence-along-ethnic-lines-6713a1920b02

10 Wilmot, Tveteraas and Drew (2021) The Media Manipulation Casebook, Available at: https://mediamanipulation.org/case-studies/dueling-information-campaigns-war-over-narrative-tigray

*“ጥቃቶች እና ትንኮሳዎች ሁለት ክፍል ነበራቸው ፣ብሔር እና ፆታ። ጥቃቱ ብሔር ተኮር ሲሆን አንድን ብሔር የሚያሳንሱ ቃላቶችን በመጠቀም የሚከናወን ነው፣ ፆታ ተኮር ሲሆን ግን ቅምጥና የመሳሰሉት ስድቦችን በመጠቀም ይደረጋሉ።”*

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ላይ ያተኮረው ይህ ጥናት የብሔር ማንነት ጉዳይን መረዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተረድቷል። ለምሳሌ የአውሮፓ ሰላም ኢንስቲቲዩት ጥቂት የቲውተር ልጥፎችን ወስዶ ባጠናው ጥናት “ብሔርተኝነት” ለብዙ ጥላቻ ንግግሮችና ለተሳሳቱ መረጃዎች መነሻ ነው በማለት አብራርተዋል።[11] በተጨማሪም “ብሔርተኛ” የሆኑ የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች “ጠብ ቀስቃሽ የሆኑ አስተያየቶችን” በማጋራትና ያለውን ክፍፍል በማባባስ አልፎም የተሳሳቱ መረጃዎችን በማሰራጨት ዙሪያ ቅሬታ ቀርቦባቸዋል።[12] ከዚህ በፊት የተጻፉ ፅሁፎች በብሔር ዙሪያ ያሉ ጥላቻ ንግግሮች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የፆታዊ ክፍሉ ላይ ግን አያተኩሩም ። በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት በማጥናት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ብሔር ተኮር ጥቃት እንደደረሰባቸው ለመረዳትና ፣ በጥቃቶቹ ባህሪ ምክንያት ተፅዕኖአቸው ሴቶች ላይ የከፋ እንደሆነ ለመመርመር ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል ።

*5.1.1.3 ፖለቲካና ግጭቶች*

የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች የፖለቲካ ምስል እየተሰጣቸው እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሰፊው ያምናሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ከ 90 በላይ የተለያዩ ብሔሮች እንደመኖራቸው የተለያዩ ስፋት ያላቸው ብሔር-ተኮር ግጭቶች በተደጋጋሚ ያነሳሉ ።[13] እ.ኤ.አ በታህሳስ 2020 በሰሜን ኢትዮጵያ የተነሳው ግጭት ብሔር ከፋፋይ ለሆኑ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች መንስኤ ሆኖ ነበር ። ከ 42 በመቶ በላይ የሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች ለትግራይ ግጭት በሰጡት የሚዲያ ሽፋን ምክንያት የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንደደረሰባቸው ተናግረዋል። ተሳታፊዎቹም በሌሎች ሀገራዊ ሁነቶች ዙሪያ ጥቃቶች ቢደርስባቸውም በትግራይ ጦርነት ዙሪያ የደረሱ ጥቃቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። ለምሳሌ አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ በግጭት ጊዜ ስለነበረው ኢንተርኔት ላይ ጥቃት ይሄን ብላለች፡

*“በትግራይ ጦርነት ዘገባ ዙሪያ የነበረው ዛቻ ለወራት የዘለቀ ፣ የማያቋርጥ እና አቆመ ሲባል እንደ አዲስ የሚጀምር ነበር።”*

በትግራይ ውስጥ ስለተፈፀመው የጦር ወንጀል ዙሪያ መግለጫ የሰጠች የጥናቱ ተካፋይ ይህንን ብላለች፡

*“ዛቻው ከሁለቱም ማለትም ከትግሬዎች እና ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የመጣ ነበር... በመቶዎች የሚቆጠሩ በጉዳዩ ላይ አስተያየት አየሰጡና እየተሳተፉ ስለነበር ለእኔ አስጨናቂ ወቅት ነበር ።”*

በመንግሰትም ሆነ በክልልና ደረጃ ማህበራዊ ሚዲያን ለፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ መድረክ እንደሆን አድርጎ የማየት አስተሳሰቦች እንዳሉ ሌላው የጥናቱ ቁልፍ ግኝት ነበር። አንድ በቃለመጠይቁ ላይ የተሳተፈች ጋዜጠኛ እንደገለፀችው

[11] European Institute for Peace (2021) Available at: https://www.eip.org/new-publication-fake-news-misinformation-and-hate-speech-in-ethiopia-a-vulnerability-assessment/

[12] Ibid.; Workneh (2019) African Journalism Studies, Available at: https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/23743670.2020.1729832

[13] Minority Groups International (n.d.) Ethiopia - World Directory of Minorities & Indigenous Peoples, Available at: https://minorityrights.org/country/ethiopia/

*"ጥቃቶቹ ግለሰብን ለማጥቃት ያለሙ አይመስለኝም ይልቁንም የራሳቸው አጀንዳ ለማራመድ ተብሎ የሚፈፀም ነው።"* በተመሳሳይ ሌላ ተሳታፊ ይህን ብላለች፡

> *"የእነሱን አጀንዳ የሚደግፍ እንቅስቃሴ ካደረኩኝ ድጋፋቸውን ይሰጡኛል ።ነገር ግን ከእነርሱ አጀንዳ ጋር የሚቃረኑ ሀሳቦችን ስዘግብ ማስፈራሪያ ድረስ የደረሰ ተቃውሞ ይደርስብኛል ።"*

ሰዎች ከደጋፊ ወደ ተቋዋሚ የሚለወጡበት ፍጥነትም በዚሁ ጥናት ላይ ታይቷል ። ይህ ሀሳብ የመረጃዎችን እውነተኛነት በምታረጋግጥ ባለሙያ ዘንድ ተነስቷል፡

> *"የአንድ ብሔር መብት ጥሰት ሲያጋጥመውና ያንን መረጃ ስትዘግቢ ከዛ ብሔር ትልቅ ድጋፍ ታገኛለች ። ይህ ድጋፍ ግን እውነተኛ አይደለም ። በአንድ ወቅት የደገፈሽ ቡድን ጥፋት ሰርቶ ይህንን ጥፋት ከተቃወምሽ አድሎአዊ ተብለሽ የፖለቲካ ሰዎች መጠቀሚያ ትሆናለች።"*

እንደ ጥናት ተሳታፊዎች ገለጻ ከጥቃት አድራሾቹ ጋር በፖለቲካ ጉዳዮች አለመስማማት ከተፈጠረ ጥቃት አድራሾቹ ፆታ-ነክ በሆነ መንገድ ጥቃት ይፈጽማሉ።

> *"አሁን ባለው አዝማሚያ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር በፖለቲካ ሀሳብ ካልተስማማሽ ፆታን መሰረት ያደረገ ስድብ ይሰድቡሻል። አስቀያሚ እንደሆንኩኝ እና በአደባባይ ለመናገር ጥሩ ፊት እንደሌለኝ ተናግሮኛል ። 'ሴተኛ አዳሪ ነሽ' 'ማንም አይፈልግሽም' የሚሉ መልዕክቶችም ደርሰውኛል።"*
> በማለት አንድ የጥናቱ ተሳታፊ ገልፃለች።

አንድ የጥናቱ ተሳታፊ በአንድ ወቅት ከአንድ የዝግጅት መሪ ጋር ስለነበራት አጋጣሚ እንደዚህ ገልፃለች *"በውይይት መሀል የምንወያይበት ጉዳይ ከባድ እንደሆነ ነገረኝ ። አስተያየቱን የሰጠበት መንገድ የጉዳዩን ክብደት ለመግለፅ ሳይሆን እኔ ላይ ያነጣጠረ ነበር።"* ይህ ሀሳብ በሌሎች ተሳታፊዎችም ተነስቷል

> *"ሰዎች በውይይት ርዕሱ ላይ መነጋገር ሳይችሉ ሲቀሩ በሴትነትሽ ይሰድቡሻል ። ሴትነትሽ እንደድክመት አይተው ሊያስፋራሩሽ ይሞክራሉ።"*

ይህም ኢትዮጵያዊያን በኢንተርኔቱ ዓለም ውስጥ የሚያጋጥማቸው መርዛማና ጤናማ ያልሆነ ሁኔታዎችን ያሳያል ። ይህ ችግር ሴቶችም ሆነ ወንዶች የሚጋፈጡት ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ጤናማ ያልሆነ የፖለቲካ ምህዳር ማንጸባረቂያ ነው። በተጨማሪም ልሂቃንና የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች የፖለቲካ አጀንዳቸው ለማረመድ ሲሉ ጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው ንፁሀን ይጎዳሉ። ሆኖም ግን ከተጠቀሱት ችግሮች ጋር በተያያዘ ወንዶች በፖለቲካ አቋማቸውና ወገንተኝነታቸው ጥቃት ሲደርስባቸው ሴቶች ግን ፆታቸውን መሰረት ያደረገና ማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ሚና ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ይደርስባቸዋል ።

*5.1.1. የግብረሰዶማዊነት ውንጀላዎች*

በተለያዩ የኢንተርኔት መድረኮች ላይ ስለሴቶች መብት የሚሟገቱ ብዙ ሴቶች የቃላት ጥቃትና የግብረ-ሰዶማዊነት ውንጀላዎች እንደሚደርስባቸው ገልፀዋል። ግብረሰዶማዊነት በኢትዮጵያ ውስጥ አንደ ነውር የሚታይ ርዕስ ከመሆኑም በላይ ህገ-ወጥና እስከ አንድ አመት በእስራት ሊያስቀጣ ይችላል። ይህ አይነቱ ጥቃት 29 በመቶ አካባቢ በሆኑ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ላይ ድረሷል። አንድ ተሳታፊ ይህን ብላለች

> *“እንደ አጠቃላይ የሴቶችን መብት ለማስከበር በማደርገው እንቅስቃሴ ምክንያት የግብረሰዶማዊነት ውንጀላዎች ይደረሱብኛል። እንደእነሱ አነጋገር ‘ወንዶችን ስለማትወጂና ስለወንዶች ብዙ ጥሩ ነገሮችን ስለማትናገሪ ከወንድ ጋር የመሆን ፍላጎት የለሽም’ ይሉኛል”*

ይህ ሀሳብ በሌሎች ተሳታፊዎች ዘንድም ተነስቷል

> *“ወንዶችን ትጠያለሽ ፣ ግብረሰዶም ነሽ፣ ወደጓዳ ተመለሺ፣ አስቀያሚ ስለሆንሽ ነው፣ ማን ካንቺ ጋር መሆን ይፈልጋል፣ ወንድ ነው የምትመስዪውና የመሳሰሉ ስድቦችና አስተያየቶችን መቀበል የተለመደ ነው። እኛን እንደ ግብረሰዶም በመሳል ግብረ-ሶዶማዊነትን ለማስፋፋት እየሰራን እንደሆነ አስመስለው የሚያሳዩ ቪዲዮዎችም ይሰራሉ።”*

አንድ የግንኙነት ባለሙያ የትዳሯን ፍቺ ግብረሰዶም እንደሆነች ለማሳየት በማስረጃነት ተይዞ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሲዘዋወር እንደነበረ ገልፃለች። ከግብረሰዶማዊነት ጋር ምንም ተያያዥነት የሌላቸውን ፅሁፎች ብትፅፍም ራሷ ግብረሰዶም እንደሆነች በማስመሰል ጥቃት እነደሚደርስባት ገልፃለች።

አንድ የመንግስት ሰራተኛ የጥናቱ ተሳታፊ ሰዎች ግብረሰዶማዊነትን ትደግፋለች ብለው በማሰብ ብቻ የደረሰባትን ጥቃትና ተያያዥ ጭንቀት እነደሚከተለው አጋርታለች

> *“በመንግስት ስር ሆነው ግብረሰዶማዊነትን ይደግፋሉ የሚባሉ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ተካትቼ ነበር። በዝርዝሩ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ግብረሰዶማዊነትን የሚያበረታታ ፖሊሲ አርቅቃችኋል በሚል የተወነጀሉ ነበሩ። ዝርዝሩም ስማችንና ፎቶግራፋችንን ያካተተ ሲሆን መንግሰት በግብረሰዶማዊነት ዙሪያ ያለውን ፖሊሲ ለማስቀየር እየሰራን እነደሆነ ተደርጎ የወጣ ነበር። ይህ እንቅስቃሴ ዘመድኩን በተባለ አክቲቪስት ተጀምሮ በመስፋፋት እኛ ላይ ወዳነጣጠረ ዘመቻ ተቀይሮ ነበር። ”*

እነዚህ ውንጀላዎች ለተጠያቂዎቹ ከፍተኛ የህልውና ስጋት ይዘው የሚመጡ ናቸው። በዚህ ቃለ-መጠይቅ ላይ የተሳተፉት ሴቶች ባያነሱትም በኢንተርኔት ላይ የሚደርሱ የግብረ-ሶዶማዊነት ውንጀላዎች መሬት ላይ የህግ ተጠያቂነት ሊያስከትሉ ይችላሉ። እንደ አንድ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ አነጋገር አንዳንድ ጊዜ የህዝብ ጥያቄን ተከትለው የሚመጡ እስሮች አሉ። ስለዚህም ውሸት የሆኑ የግብረ-ሶዶማዊነት ውንጀላዎች ያለመረጃ ለእስር ሊዳርጉ ይችላሉ። በተጨማሪም ግብረ-ሶዶማዊነት በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ሀሳብ እንደሆነና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች አንኳን ስለ ጉዳዩ አንደማያነሱ ተገልጿል።

*5.1.1.5 ሃይማኖት*

ከ21 በመቶ በላይ የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች፣ ጥቃት ፈጻሚዎች፣ ሃይማኖትን እንደሽፋን ተጠቅመው ጥቃት እንዳደረሱባቸው ገልፀዋል። ለምሳሌ አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በኩል በተዳረች የ12 ዓመት ሴት ልጅ ዙሪያ ባሰማችው ተቃውሞ ምክንያት ከአንድ ሴት ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ የደረሰባት ጥቃት አንዳሳዘናት *ገልፃለች። “ስለ ፆታ ነክ ጉዳዮች በመናገርሽ በሴቶች በራሳቸው ጥቃት ሲደርስብሽ ሀዘኑን የከፋ ያደርገዋል”* በማለት ሀሳቧን አጋርታለች። በሌላ ቃለ መጠይቅ ላይም ተመሳሳይ ሀሳብ

ተጋርቷል። በሴቶች መብት ላይ የሚሰራ ድርጅት ውስጥ እንደ ግንኙነት ሀላፊ ሆና የምትሰራ ባለሙያ፣ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ ባትገባ አንኳ ጥቃቶች እንደሚደርሱባት ትናገራለች

*"በአንድ ወቅት አንዷት የ 12 ዓመት ልጅ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ለነበረና ለአቅመ አዳም ለደረሰ ሰው መዳሯ በትዊተር መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ከዚያም ፖሊስና ፍርድ ቤት በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት ትዳሩ ፈርሶ ሰውየውም ለህግ እንዲቀርብ ተደረገ። አንዳንድ የቲውተር ተጠቃሚዎች ያለእድሜ ጋብቻ የሚለውን ቃል በመጠቀምና ሃይማኖታቸውን በመንካት በሚሉ ሀሳቦች ወንጅለውን ነበር። የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ለማዋረድ እና ሃይማኖታችንን ለማጥቃት ከፖሊስና ፍርድ ቤት ውሳኔ ጀርባ የእናንተ እጅ አለበት የሚሉ ውንጀላዎች ነበሩ "*

ሌላ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ደግሞ የሴቶችን መብት ለማስክበር ባደረገችው እንቅስቃሴ ምክንያት በሃይማኖት ሽፋን በዛ ያሉ ጥቃቶች የደረሰባትን ጊዜ እንዲህ አስታውሳለች፡

*"በአብዛኛው ማሕበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው የሚችል ጉዳይ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ላይ አጋራሁ። ያጋራሁትም መልዕክት 'በሴቶች መብት ዙሪያ ሃይማኖት ላይ እምነት የለኝም። ልጆቼን ከማንኛውም ቤተ-እምነት ተፅዕኖ ውጪ አድርጌ ማሳደግ የምፈልገው ለዛ ነው' ይል ነበር። 'ልጆቼን በአንድ ሃይማኖት ገድቤ ሌሎች ሃይማኖትን እንዲጠሉ ከመድረግ ይልቅ ሲያድጉ መከተል የሚፈልጉትን ሃይማኖት ይመርጣሉ' በማለት ገለፅኩ። ስቀጥልም እኔ ዛሬ ታጋሽ እና ነፃ የሆንኩት ወላጆቼ እንደዛ አድርገው ስላሳደጉኝ ነው አልኩኝ። ሆኖም ግን ይሄ መልዕክቴ እጅግ በጣም አሉታዊ የሆኑ መልዕክቶች እንዲደርሱኝ አድርጓል። ጉዳዩን ከሴትነቴ፣ የግል ህይወቴ እንዲሁም ከወሣሠሉ ነገሮች ጋር አገናኝተውት ነበር።"*


በሌላ ቃለ መጠይቅ ላይ አንድ ጋዜጠኛ ከሃይማኖት ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ አስታያየት ከመስጠት እንደምትቆጠብና ይህን ማድረግ ሞትን እንደመመኘት ነው ስትል ገልፃለች። ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ይልቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ስትሳተፍ የተሻለ ደህንነት እንደሚሰማት አክላለች።

የጥናቱ ተሳታፊዎች ሃይማኖትን እንደ ብሔርና ፖለቲካ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ባያነሱትም በሃይማኖትና በመሰል ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ኢንተርኔት ላይ ውይይት ማድረግ ጥቃቶችን የመጨመር ዕድል አለው። ወንዶችም ሆነ ሴቶች በሃይማኖት ሽፋን ጥቃት ቢደርስባቸውም ሃይማኖትና የሴቶች መብት በሚጋጩበት አካባቢ ላይ ስለሴቶች መብት መስበክ አስቸጋሪ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷታል። ይህም ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ከፆታ አንፃር ያለውን ግንኙት ለመረዳት ተጨማሪ ጥናች እንደሚያስፈልጉ ያሳያል ።

## 5.1.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች

የተደረጉት ቃለ መጠይቆች የኢትዮጵያ ሴቶች እየገጠማቸው ያለውን የተለያዩ አይነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት የደረጉ ፆታዊ ጥቃቶችን ዳስሷል። ስድብ፣ ማስፈራሪያና ዛቻ በቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በአብዛኛው የተጠቀሱ የጥቃት አይነቶች ሲሆኑ ትንኮሳና የስም ማጥፋት ደግሞ ቀጣዩን ደረጃ ይያዛሉ። ሁለት ሴቶች ኢንተርኔት ላይ በሰፊው ሲዘዋወር የነበረ የስዕላዊ ቀልድና ክብርን ዝቅ የሚያደርግ የቪድዮ ሰለባ እንደነበሩ አጋርተዋል።

ብዙ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች የአካላዊ ጥቃት፣ የመደፈርና የእስር ዛቻዎች እንደደረሰባቸው ገልፀዋል። በተጨማሪም አንድ የቴሌቪዥን ዝግጅት አቅራቢ መንግስትን የሚቃወሙ መረጃዎች ከመዘገብ እንድትቆጠብ ማስፈራሪያ እንደደረሰባት ተናግራለች።




*ምስል 2: ሴቶች የደረሱባቸው የኢንተርኔት ላይ ጥቃት አይነቶች*

የመድፈር ዛቻዎች በብዙ ተሳታፊዎች የተነሳ ጉዳይ ነው። አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ልጆቿን የመድፈር ማስፈራሪያ መልዕክቶች  በፌስቡክ አስተያየት መስጫ ላይ እንደደረሷት አስረድታለች። አንድ ጋዜጠኛ ሀሳቧን እንደዚህ አጋርታለች *"ስለ ሴቶች መብት በምንወያይበት ጊዜ የአስገድዶ መድፈር ዛቻዎች ይጨምራሉ።"* ሌላ ቃለ መጠይቅ ላይ አንድ የቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሚከተለውን ብላለች፡

> *"መንገድ ላይ ብናገኝሽ እንደበድብሽ ነበር፣ አሲድ ፊትሽ ላይ እንደፋብሻለን፣ አስገድደን እንደፍርሻለን አልፎም እኔና ጓደኞቼ ባንወድሽም ቆንጆ ስለሆንሽ በቡድን እንደፍርሻለን የሚሉ ዛቻዎች ይደርሱኛል።"*

ብዙ ሴቶች የሞት ዛቻ እንደሚያደርስባቸውም ገልፀዋል። አንድ የቴሌቪዥን ዝግጅት አቅራቢ *"አንቺን ገድዬ ነው የሚሞተው"* የሚል እና ሌሎች የመሳሰሉ ዛቻዎች በሁሉም የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ያለማቋረጥ እንደሚደርሳት ገልፃለች

የግል ሚስጥር ያለፍቃድ ለህዝብ ይፋ ማድረግን ጨምሮ ሌሎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በግልና በቤተሰብ ህይወታቸው ላይ ጫና እንደተፈጠረባቸው የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አጋጣሚ መታሰሯን ስትገልፅ ሌላ ተሳታፊ ከእስር ለማምለጥ ከሀገር እንደተሰደደች ተነግራለች። (ክፍል 5.4 ይመልከቱ) አንድ ጋዜጠኛ መታሰሯን የሚደግፍና *"የምትደበቂበት ቦታ ያለ መስሎሻል እስር ቤት ገብተሽ ትገረፊያለሽ"* የሚል ተደጋጋሚ ዛቻዎች እንደደረሷት ገልፃለች

አንድ ጋዜጠኛ ከእስር ጋር ስለተያያዙ ዛቻዎች ስትናገር ይህን ብላለች

*"...የገረመኝ ነገር ቢኖር በሚዲያ አለም ውስጥ ታላላቅና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ግለሰቦች የኔን መታሰር የሚደግፈውን ዘመቻ ሲደግፉ ነበር። በምን ምክንያት ይህን ልያደርጉ እንደነበር አልገባኝም። እነሱ የማይወዱትን ሰው ቃለ መጠይቅ ስላደረኩ ነው? ከቁምነገር ባልወሰዳቸውም የሞት ዛቻዎች ይደርሱኝ ነበር። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እንድታሰር ከመናገርም አልፈው አስር ቤት ውስጥ እንድደፈር፣ እንድደበደብና እንድሞት ምኞታቸውን ገልፀዋል።አስገድዶ መድፈር በኢትዮጵያውያን ወንዶች ዘንድ አንድ ማጥቂያ መሳሪያ መታሰቡ አሳዛኖኝ ነበር።"*

በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰሩ ድህረ-ገፅና ጋዜጣ የመሠረተች አንድ ሴት፣ በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገጾች ላይ ሴቶች ስለሚገጥማቸው ጥቃት በተደጋጋሚ መረጃ እንደሚደርሳት ተናግራለች። እነዚህም ብዙውን ጊዜ ሚስጥራዊነት ያለው መረጃ እንደሚለቁ ማስፈራሪያዎችን ያካትታሉ።

*"ለምሳሌ የድርጅታችን ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ጥቃትና ትንኮሳ የደረሰባቸውን ሴቶች መልዕክት በብዛት ይቀበላሉ። አብዛኞቹ ሴቶች እነዚህ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች በቴሌግራምና በኢንስታግራም እንደደረሰባቸው ይናገራሉ። ከቀድሞ ፍቅረኞቻቸውና አፈቀርናቹ ከሚሉ ወንዶች ዛቻ እንደደረሰባቸውም አስረድተዋል። ሚስጥራዊ ፎቶዎችና ከዚህ በፊት የተላላኳቸውን የፅሁፍ መልዕክቶቸን ይፋ እናደርጋለን የሚል ማስፈራሪያ እንደሚደርስባቸው አስረድተዋል ። በዚህም ምክንያት አሳሳቢ በሆነ ሁኔታ ብዙ ሴቶች እነዚህን ችግሮች ይዘው የእኛን እርዳታ ጠይቀዋል።"*

በቃለ መጠይቁ የተሳተፉት ሴቶች የደረሱባቸውን ዛቻዎች ይዘትም ሆነ በክብደት የተለያዩ ናቸው። ይህ የመታሰር ዛቻና ማስፈራሪያ ወንዶችንም የሚነካ ቢሆንም የመደፈር ዛቻዎች ግን ሴቶች ላይ ብቻ በብዛት ይታያል።

## 5.1.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ ድግግሞሽና መጠን

ሁሉም የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እየበዙና ፅንፍ እየያዙ መምጣታቸውን ገልፀዋል። እንደ ቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎቹ ገለፃ ኢንተርኔት ላይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶች በአንድም ሆነ በሌላ ጊዜ ኢንተርኔት ላይ ጥቃት ደርሶባቸዋል። እነዚህም ጥቃቶች ሴቶች ሀሳባቸውን እንዳይገልፁ፣ ዝምታን እንዲመርጡና ከተለያዩ ህዝባዊ መድረኮች አንዲገለሉ አድርገዋል (ክፍል 5.4 ይመልከቱ)

አብዛኞቹ የቃለ-መጠይቁ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የደረሰባቸው ባሳተሙት ፅሁፎች፥ በተሳተፉበት ዝግጅት ወይም ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገጾች ላይ ባጋሩት ልጥፍ እነደሆነ ገልፀዋል። ሆኖም ግን 14 በሙቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች የደረሱባቸው ጥቃቶች ይህ ነው የሚባል ምክንያት ጋር እንደሌላቸውና ቀን ተቀን የሚከሰት አንደሆነ ተናግረዋል። ለምሳሌ አንድ የቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪ ይህን ብላለች *"ጥቃቶቹ ያለማቋረጥ ይደርሱ ነበር፤ ይህ ሳይሆን አንድም ያለፈ ቀን የለም።"* በተመሳሳይ እንዲት ሴት ጋዜጠኛ ይህን ብላለች

*"የኢንተርኔት ላይ ትንኮሳና ጥቃት የቀን ተቀን ሁነቶች እየሆኑ ነው። ሰዎች ስድቦችንና ዛቻዎችን ይፅፋሉ። የፃፍሽውን ሀሳብ እንዲትሰርዢና በፃፍሺው ነገር እንዲትፀፀቺ ይነግሩሻል።"*

በአንዳንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች መሠረት ወንዶችና ሴቶች በአይነት የተለያየ ጥቃቶች ከማስተናገዳቸው በተጨማሪ ጥቃቶቹ በመጠንም እንደሚለያዩ ገልፀዋል። በዩቲዩብ ላይ ዝግጅት አቅራቢ የሆነች አንዲት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ የስድብና የማስፈራሪያ አስታያየቶች እንደሚደርሷት ገልፃለች። የምታቀርበው ዝግጅት ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መሆኑ ለእንደዚህ አይነት አስተያየቶች መቀበል ምክንያት እንደሆነ ብታምንም ከወንድ የስራ ባልደረባዋ በዛ ያለ ጥቃት እንደሚደርስባትና እንዲሁም ጥቃቶቹ በመልኳ ዙሪያ እንደሚያጠናጥኑ ገልፃለች

> *"ዝግጅቱ ፖለቲካዊ ይዘት ስለነበረው ሀሳቦቼን ከመሞገት ይልቅ እኔን ማጥቃት ቀሏቸው ነበር መሠለኝ። ሴት መሆኔ ደግሞ ለጥቃቱ ኢላማ እንዲሆን ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም በፍርሃትና የእነሱን አስተያየቶች በመስማት ዝግጅቱን አቋርጣለሁ ብለው አስበውም ይሆናል ምክንያቱም የሠጡኝ አስተያየቶች ካቀረብኩት ዝግጅት ጋር የሚገናኝ አልነበረም።"*

ይህ ሀሳብ ግን በሁሉም ተሳታፊዎች ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ወንድ የስራ ባልደረባዋ አካባቢዋ ካሉ ሰዎች በሙሉ የበለጠ ዛቻና ማስፈራሪያ እንደሚደርስበት ተናግራለች። ይህ የስራ ባልደረባዋም ትንሽ ቆይቶም እንደታሠረና እሷም እስርን ሽሽት ከሀገር ለቃ እንደሄደች ገልፃለች። ከወንዶችና ከሴቶች ማን ብዙ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ይደርስበታል በሚለው ሀሳብ ዙሪያ የተለያዩ ሀሳቦች ቢኖሩም የኢንተርኔቱ ዓለም ለሁለቱም ፆታዎች ጤናማ እንዳልሆነ ግልፅ ነው።

## 5.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የሚፈፀሙባቸው መድረኮች

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የሚሰነዘርበትን መድረክ ለመመርመር አልሞ የተነሳ ነው። ይህም የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ዙሪያ ትንተናን፣ ጥቃቶች የሚደርሱበት ቦታዎችን መለየትን፣ ጥቃቶቹ በቀጥታ የመልዕክት መሰመር ወይም አደባባይ በሆኑ ጣቢያዎች ላይ መካሄዳቸውን ማጣራትና ጥቃቶቹ ከኢንተርኔት ውጪ በዋና ሚዲያዎች ላይ መታየታቸውን መመርመርን ያካተተ ነበር። ፌስቡክ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የሚፈፀምበት ዋና መድረክ ቢሆንም በሌሎችም የሚጠቀሙት ማህበራዊ ትስስር ድህረገፆች ላይ ጥቃቶች እንሚደርሱባቸው ሴቶች ተናግረዋል።

### 5.2.1 የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች አጠቃቀም


በቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉ ሴቶች ንቁ ተሳትፎ በሚያደርጉባቸው ማህበረዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ጥቃት እንደደረሰባቸው ገልፀዋል። የጥናቱ ተሳታፊዎች በአብዛኛው ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኤክስ እና ዋትሳፕ ተጠቃሚዎች ናቸው። እንደ ማስቶዶን እና ቲክቶክ ያሉ አዳዲስ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ደግሞ ትኩረትን እየሰቡ መጥቷል።

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎቹ የተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆችን ለተለያየ አላማ እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል። ማህበራዊ ሚዲያን ለመረጃ ምንጭነት፣ ሀሳባቸውን ለማጋራት፣ ስራቸውን ለማስተዋወቅ፣ ለመዝናኛ፣ በጉዳዮች ላይ ድምፃቸውን ለማሰማት ወይም ከዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋር ለመገናኘት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል። አንድ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ላይ ዝግጅቶችን የምታቀርብ ሴት፣ ማህበራዊ ሚዲያን ከሴቶች መብት ጋር በተያያዘ ያሏትን ሀሳቦች ለማካፈል የምትጠቀምበት ትልቅ መድረክ መሆኑን ገልፃለች። ሆኖም ስለተለያዩ ማህበራዊ

ትስስር ድህረ ገፆችና ጥቅሞቻቸው በተወያየንበት ወቅት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ስለተስፋፋው በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ፆታዊ ጥቃት ዙሪያ ያላቸውን ስጋት ተሳታፊዎቹ አጋርተዋል።

ከጥናቱ ውጤት አንዱ ትኩረት ሳቢ ጉዳይ ማስቶዶን በተባለውና 21 ከመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች በሚጠቀሙት መህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ዙሪያ ያለው አመለካከት ነው። አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ማስቶዶን ከሌሎቹ መህበራዊ ትስስር ድህረ ገፅ በተሻለ ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ይሰማታል። በተጨማሪም ማስቶዶን *"ብዙ ጋዜጠኞች የሚጠቀሙትና ትኩረትን የሚስቡ ፅሁፎች የሚያጋሩበት ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ነው"* ብላለች። ሌላ የቃለ-መጠይቁ ተሳታፊ ተዊተር መጥፎ ቦታ እየሆነ ስለመጣ ማስቶዶንን መጠቀም እንደመረጠች ተናግራለች።

እንደ ቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገለፃ በሀገሪቱ ውስጥ በሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች መንግስት የሚጥላቸው የማህበራዊ ሚዲያ እገዳዎች፤ ግለሰቦች አማራጮችን ፍለጋ የተለያዩ አይነት የማህበራዊ ሚዲያዎችን እንዲጠቀሙ እንዳደረገ ገልፀዋል። ብዙ ተሳታፊዎች በዋትሳፐ ደስተኛ ስላልሆኑ ሲግናል የተባለውን ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ መጠቀም እንደጀመሩ ገልፀዋል።አንድ የቃለ-መጠይቁ ተሳታፊ ወጣቶችን መሠረት ያደረገ መልዕክት ለማስተላለፍ ስታስብ ቴሌግራምን እንደምትጠቀም ገልፃለች። ይህም የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያየ አይነት ማህበራዊ ሚዲያ እንደሚጠቀሙና በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን ወቅት ይህን ከግምት ማስገባት እንዳለብን ያሳያል።




*ምስል 3: በቃለ-መጠይቁ ተሳታፊዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች። ፐርሰንቱ የእያንዳንዱን ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ተጠቃሚ ብዛት ያሳያል። ከአንድ እስከ አስር ደረጃ ያሉት ተዘርዝረዋል*

## 5.2.2 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረተ ያደረጉ ጥቃቶች የሚፈፀሙባቸው መድረኮች

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በአብዛኛው ፌስቡክን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የሚፈፀምበት ዋነኛው ማህበራዊ ትስስር ድህረ ገፅ አድርገው ሲጠቅሱ ትዊተር ደግሞ ሁለተኛውን ደረጃ ይዟል። ብዙ ሴቶች ቲክቶክ፣ ዩቲዩብ፣ ፌስቡክ፣ ትዊተርና ኢንስታግራም ላይ ያሉ አስተያየት መስጫዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ላደረገ ጥቃት መናህሪያ እንደሆኑ ገልፀዋል።

በተጨማሪ አንድ የዩቲዩብ ፕሮግራም አዘጋጅ ለሀሳብ መስጫ በሚል ያዘጋጀችው የስልክ መስመር በትንኮሳ መልዕክቶች እንደሚጥለቀለቅ ገልፃለች። በተጨማሪም ይህን ብላለች፡

> *"ሌላ በዋነኝነት ትንኮሳ የሚፈፀምበት መድረክ ፌስቡክ ሜሰንጀር የተባለው መተግበሪያ ነው። ይህም የሆነው ድርጊቱን በሚፈፅሙበት ጊዜ ማንነታቸውን መደበቅ ስለሚችሉ ነው። በፌስቡክ ላይ ሀሳብ አጋርተሽ እንደጨረሽ በግል መልዕክት መቀበያ ሳጥንሽ ውስጥ ስድቦችን ታገኛለሽ። ዝግጅቶቻችንን ካጠናቀቅን በኋላ እንኳ በአስተያየት መስጫዎች ላይ ዛቻዎች ይደርሱብናል። ሁሉም ባይሆኑ ይህንን የሚያደርጉ አብዛኛዎቹ ግለሰቦች ማንነታቸውን ግልፅ አያደርጉም።"*

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ማንነትን የመደበቁ ጉዳይ በተለያዩ ቃለ መጠይቆች ላይ ተነስቷል። በሴቶች መብት ላይ የሚሰራ የሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ እንደግንኙነት ባለሙያ ሆና የምትሰራ አንዲት ሴት ይህን ብላለች። *"ሰዎች አስተያየት ሲሰጡ ማንነታቸውን መደበቅ መቻላቸው የፈለጉትን የመናገር ስልጣን ይሰጣቸዋል፤ ለሚናገሩት ነገርም አይጠነቀቁም።"*

በጉዳዩ ላይ የተሰሩ ጥናቶች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በግልፅ የሚታዩ ጥቃቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን በግል መልዕክቶች ወይም ዝግ በሆኑ መድረኮች ላይ ባሉ ጥቃቶች ዙሪያ የተሰሩ ብዙ ጥናቶች የሉም። ፌስቡክ፣ ሜሰንጀር፣ ዋትሳፕ እና ቴሌግራም የግል መልዕክት መለዋወጫ እንደመሆናቸው መጠን በእነዚህ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ዙሪያ ጥናት ማካሄድ፣ ጥቃቶችን መቆጣጠርና ምላሽ መስጠት አስቸጋሪ ነው። ቃለ መጠይቆቹ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናቶች ሊሰጡን ያልቻሉትን መረጃዎች በጨረፍታም ቢሆን ይሰጡናል። ለምሳሌ አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ የግል መልዕክት መቀበያዋ ላይ ስድቦች፣ ጥላቻ መልዕክቶች፣ ዛቻዎች፣ ወሲባዊ የሆኑ ምስሎች እንደሚደርሷት ገልፃለች።አንድ የፖለቲካ ፀሀፊ ይህን ብላለች፡

> *"በፌስቡክና በትዊተር የግል መልዕክት መቀበያዬ በኩል ፆታን መሠረት ያደረጉ ስድቦች ይደርሱኝ ነበር። በትዊተር ከሚደርሱኝ በመቶዎች የሚቆጠሩ መልዕክቶች ውስጥ ጥሩ መልዕክት ያዘሉት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው። የተቀሩት በሙሉ ፆታን መሠረት ያደረጉ ስድቦች ናቸው። አስገራሚው ነገር አነዚህ ስድቦች ካነሳሁት ነጥቦች ጋር ተያያዥነት የሌላቸውና ፆታዬን መሠረት ያደረጉ ናቸው።"*

ሁሉም በሚባል ሁኔታ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ሴቶች በማህበራዊ ሚዲያ መተግበሪያዎች ላይ የግል መልዕክትን እንዳይቀበሉ የሚያደርግ አማራጭ ቢኖር እነዚህ ጥቃት ያዘሉ መልዕክቶች እንዳይደርሷቸው ለማድረግ እንደሚረዳ ገልፀዋል።

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያሉ መልዕክት የሚተላለፍባቸዉ መንገዶች በተጠቃሚዎቹ ላይ ያለዉን ተፅዕኖ ለማየት ተሞክሯል። ለምሳሌ አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ በፌስቡክ ላይ ያሉት *'ዜናዎች'*እና የሚሰጡት አስተያየቶች ጭንቀት ስለፈጠረባት ፌስቡክን በአጠቃላይ መጠቀም እንዳቆመች ተናግራለች ። ሌላ ተሳታፊ *'ክለብ ሀዉስ'* የተባለዉን ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ በቡድን ጥቃቶች የሚፈፀምበት መድረክ እየሆነ ስለመጣ መጠቀም እንዳቆመች ገልፃለች ።

በሴቶች ላይ የሚደርሰዉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በግል መልዕክትም ሆነ በማህበራዊ መድረኮች ላይ መድረሱ ችግሩ ማህበረሰባዊ እንጂ የአንድ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ድክመት እንዳልሆነ ያሳያል።

### 5.2.3 ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ውጪ ባሉ ሌሎች ዋና ሚዲያዎች ላይ ይታያል?

ከ42 በመቶ በላይ የሚሆኑት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚታዩት አስተሳሰቦች ከማህበራዊ ሚዲያ ዉጪ ባሉት ዋና ዋና ሚዲያዎች ላይም እንደሚንፀባረቅ ገልፀዋል። አንድ ጋዜጠኛ ተሳታፊ እንደገለፀችዉ በኢንተርኔት ላይ የሚነገሩ ሃሜቶችና ጥቃቶች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን እና በሌሎች ሚዲያዎችም ላይ መነጋገሪያ ይሆናሉ። በዋና ሚዲያዎች ላይ ጥቃት የደረሰባት አንድ የቃለ-መጠይቁ ተሳታፊ ይህን ብላለች

> *“መንግስት በሰዎች ዘንድ ተሰሚነት እንዳይኖርሽ ሲፈልግ ወይም መንግስት እንዲነገር የሚፈልገዉን ብቻ እንድትናገሪ ሲያስብ በዋና ሚዲያዎች ላይ ያጠቃሻል። ይህም ወንጀለኛ እንደሆንሽ አድርጎ በመሳል የሚከናወን ነዉ። ይህ አሁንም እየሆነ ያለና በምክር ቤት ስብሰባዎች ላይም የሚታይ ነዉ። ለሀገር አደገኛ የሆኑና የብሔር ክፍፍልን የሚሰብኩ ሚዲያዎችን በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ፈቅዶ እዉነትን የሚናገሩ ጋዜጠኞችን ማጥቃት እየተለመደ መጥቷል”*

በተመሳሳይ አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ዋና ዋና ሚዲያዎች በህዝብ ስሜቶች ዙሪያ ያላቸዉን አቋም እንዲህ ገልፃለች፡

> *“የመንግስት ሚዲያዎች ከብዙሃኑ ጋር የመወገን አዝማሚያዎችን ያሳያሉ። በብዙዎች ዘንድ የማይወደድ ግለሰብ ካለ ስለዛ ግለሰብ መጥፎ ነገሮችን በዋና ዋና ሚዲያዎች ላይ እንሰማለን”*

እንደ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ሁሉ ዋና ሚዲያዎች ላይም የወንዶች የበላይነት ይስተዋላል። ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴትን አሳንሰዉ የሚያዩ አስተሳሰቦች በሴቶች የሚቀርቡ ዜናዎች ላይ ያላቸዉ ተፅዕኖ ሴቶች በሚዲያዉ ዘርፍ ሰብረዉ እንዳይገቡ እክል ሆኗል።[14] በአጥኚዎች መሰረት ሴቶችን በዉሳኔ ሰጪነት ጨምሮ በሚዲያ እንዱስትሪዉ እንዲሳተፉ ማበረታት ሴቶች በሚዲያዎች ላይ የሚወከሉበት መንገድ ለማሻሻልና ያለዉን የፆታ መገለል ለመቀነስ ይረዳል።[15] ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት የሴቶችን ማህበራዊ ተሳትፎ መጨመር በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚወከልበትን መንገድ ያሻሽላል ። ሆኖም ግን በዚህ ጥናት ላይ የታዩት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃቶችና ሴትን አሳንሰዉ የሚያዩ አመለካከቶች ከኢንተርኔት ላይ በተጨማሪ ከኢንተርኔት ዉጪም የሴቶች መብት ላይ አተኩሮ መስራት እንደሚያስፈልግ ማመላከቻ ናቸዉ።

[14] Mengistu (2007) Addis Ababa University, Available at: http://etd.aau.edu.et/handle/123456789/5375

[15] Kassa and Sarikakis (2022) Feminist Media Studies, Available at: https://www.tandfonline.com/doi/epdf/10.1080/14680777.2021.1917640

## 5.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዓላማ

በዚህ ጥናት ከጥቃቶቹ ጀርባ ያሉትን ዓላማዎችና ጥቃቶቹ በተቀናጀ ሁኔታ እንደሚካሄዱ ለማወቅ ተፈልጎ ነበር። ሴቶችን ዝም ማሰኘትና የወንዶችን የበላይነት ማስቀጠል በቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች እንደ ጥቃት ዓላማዎች የተቀመጡ ሀሳቦች ናቸዉ። ጥቃቶቹ በተቀናጀ ሁኔታ ስለመካሄዳቸዉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያሉት ነገር የለም። ሲ.አይ.አርም ይሄንን ለማጣራት ሙከራ አላደረገም።

### 5.3.1 የጥቃቱ ፈፃሚዎች ግብ

የጥናቱ ተሳታፊዎች የጥቃት ፈፃሚዎቹን ግብ ሲጠየቁ የተለያዩ ምክንያቶችን ገልፀዋል። ከምክንያቶቹም ውስጥ ሴቶችን ለማዋረድ፣ ለማስፈራራት ወይም ዝም ለማሰኘት እና አጥቂዎቹ ስለራሳቸዉ ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸዉ ለማድረግ እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል። ለምሳሌ በቲክቶክ ላይ ስለሴቶች መብት የምትሟገት አንዲት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ይህንን ብላለች፡

> *"ጉዳዩ ከሀይል ሽኩቻ ጋር የተገናኘ ይመስለኛል። ብዙ ወንዶች የምንናገራቸዉ ነገሮች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸዉን ቦታ ዝቅ የሚያደርግባቸዉ ይመስላቸዋል። መብታቸውን እንደነካሁባቸዉ አድርገዉ ያዩታል"*

50 በመቶ የሚሆኑት ጥቃት ፈፃሚዎቹ ሴቶችን ዝም ለማስባል አስበዉ ጥቃት እንደሚፈፅሙ ገልፀዋል። (ይህ በክፍል 5.4 በሰፊዉ ይታያል) አንድ የሴቶች መብት ተሟጋች ይህንን ብላለች፡

> *"ጥቃት ፈፃሚዎቹ ይህንን የሚያደርጉት እኔን ዝም ለማሰኘት እንደሆነ አምናለሁ ደግሞም ተሳክቶላቸዉ ነበር። ብዙ ሴቶች ስለመብታቸዉ እንዲናገሩ አነሳስተናል። ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ስለ አስገድዶ መድፈር፣ ፆታዊ አድሎ እና ስለሴቶች መብት ቪዲዮዎች እንዲሰሩ አስማምተናል። ነገር ግን የሚደርሳቸዉን ዛቻና ማስፈራሪያ መቋቋም ሳይችሉ ቀርተዉ ቪዲዮችን ያወርዱታል፤ ስለ ጉዳዩም መናገር ያቆማሉ። የጥቃት ፈፃሚዎቹ ፍላጎት እኛን ዝም ማስባል ነዉ። 'ዝም በሉ ፣ መቼ ነዉ ዝም የምትሉት፣ የመናገር መብት የላችሁም፣ ልጅ ሳይኖራችሁ ስለ ቤት ዉስጥ ጥቃት መናገር አትችሉም' የሚሉ መልእክቶች ይደርሱናል።"*

አብዛኛዎቹ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች የደረሰባቸዉ ጥቃት ፆታዊ ቢሆንም ከጀርባዉ የፖለቲካና ብሔር ነክ አጀንዳን ማራመድ እንደ ግብ ያነገበ ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል። (በክፍል 5.1.1.3 እንደተገለፀው) ለአብዛኛዎቹ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች የጥቃት አድራሾቹ ግብ ግልፅ አይደለም። የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ ግን ገልፀዋል

> *"የአብዛኛዎቹ ጥቃትና መነሻ ፖለቲካዊ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን ሀሳቡን ከመሞገት ይልቅ ቀላሉን መንገድ በመምረጥ ፆታ ነክ የሆኑ ጥቃቶችን ይፈፅማሉ ። ሴቶች ሲናገሩ የማይወዱና ሴቶችን ዝም ማሰኘት የሚፈልጉም እንዳሉ ይሰማኛል። ይህም ትልቅ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ለምን ማህበራዊ ሚዲያን እንደምትጠቀሚ ሁላ ራስሽን መጠየቅ ትጀምሪያለሽ።"*

በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ አንድ ጋዜጠኛ የአጥቂዎቹ አላማ ምክንያ-የለሽ ጥቃት መፈጸም እንደሆነ ገልጻለች።

> *"ሊቀልዱብሽና መልስሽን ላለመስማት ይሞክራሉ። በመጀመሪያ በልዩነቶቻችን ላይ በመነጋገርና መረጃዎችን በማምጣት ወደ መስማማት እንመጣለን ብዬ ነበር። ሆኖም ለመነጋገር ፍላጎት እንደሌላቸዉና አላማቸዉ ጥቃት መፈፀም ብቻ እንደሆነ ተረድቻለሁ"*

ሌላ ተሳታፊ ደግሞ ጥቃት ፈፃሚዎቹ ጥቃቱን የሚፈፅሙት የሰዎችን ትኩረት ለመሳብና ብዙሃኑ የሚስማማበትን ሀሳብ በማራመድ ተከታይ ለማፍራት እንደሆነ ተናግራለች ።

ግማሽ የሚሆኑት ተሳታፊዎች የተሳሳቱ መረጃዎች በህብረተሰቡ ዉስጥ ትልቅ ሚና ያላቸዉ ሴቶችን ስም ለማጠልሸት ምክንያት እንደሆኑ ገልፀዋል ። እንደ አንድ ጋዜጠኛ *"ባለማወቅ ወይም ሆን ተብሎ የሚለቀቁ የተሳሳቱ መረጃዎች የሴት ሪፖርተሮችን ስም ለማጥፋት አንድ መሳሪያ ናቸዉ።"*

በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰራ  የአንድ ሲቪል ማህበረሰብ ዳይሬክተር ድርጅቷ በተደጋጋሚ ስለገጠመዉ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚከተለዉን ብላለች፡

> *"የተለያዩ ስድቦች በትዊተር ይደርሱኝ ጀመር። ይህም ማህበራዊ ሚዲያ እንዴት ጦር ሜዳ ሊሆን እንደሚችል ገባኝ። ቢሯችን መጥተዉ የማያዉቁ ግለሰቦች እንኳ ስለ ድርጅታችን የተፈበረኩ መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ማጋራት ጀመሩ። በቢሯችን ዉስጥ ብሔር ተኮር ጥቃት እንደደረሰባቸዉ ገለፁ። በዚህ ጊዜ ትዊተር ሀሰተኛ መረጃ ማሰራጫ ብቻ ሳይሆን የማጥቂያ መሳሪያም እንደሆነ ገባኝ። ይቅርታ ለመጠየቅ በማሰብም ጥቃቱ ተፈፀመብን ያሉት ግለሰቦች ስለ ጉዳዩ ዝርዝር መረጃ እንዲሰጡ በይፋ ጠየቅን። በአንድ ወቅት ስለእኛ ምንም መረጃ የሌለዉ ግለሰብ ሴቶች ፍቺ እንዲፈፅሙ እንደምናበረታታና የለጋሾችን ገንዘብ ዉስኪ ለመጠጣት እንደምንጠቀምበት የሚገልፅ ፅሁፍ ደርሶናል።"*

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በህይወታቸው ያጋጠሟቸዉ ሁኔታዎችና ጥቃት ለመፈፀም ምክንያት ናቸዉ ያሏቸዉ ነገሮች ተመሳሳይነት አላቸዉ ። ምክንያቶቹም ሴቶችን ለማሸማቀቅ፣ዝም ማሰኘትና ስም ማጠልሸት ናቸዉ ።

### 5.3.2 የጥቃት ፈፃሚዎቹ ማንነት

አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በኢንተርኔት ላይ ጥቃት ካደረሱባቸዉ ግለሰቦች ጋር ትዉዉቅ የላቸዉም። አንዳንድ ጊዜ ግን ትዉዉቅ ካላቸው ሰዉ ወይም ታዋቂ ከሆነ ግለሰብ ጥቃት እንደደረሰባቸዉ ገልፀዋል። ጥቃት የፈፀመባቸዉ ግለሰብ ቆይቶ ማንነቱ እንደታወቀም ያጋሩ ተሳታፊዎች አሉ። ለምሳሌ አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ይህን ብላለች፡

> *"እኔ ላይ ጥቃት ሲፈፀም የነበረ አካዉንት ጓደኛዬንም እያስቸገሯት እንደሆነ አወቅን። ቆይተንም አካዉንቱ የቀድሞ ስራ ባልደረባችን እንደሆነ ተረዳን ። እኔ እንደማስበው ምናልባት ተናግሮ ሊያናግርንና ሚስጥራዊነት ያለው መረጃ እንድናወጣ ሊያደርገን ወይም ወጥመድ ውስጥ ሊያስገባን ፈልጎ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።"*

በአንድ ቃለ መጠይቅ አንድ የኢንተርኔት ጦማሪ ጥቃቶቹን የሚፈፅሙት የዉሸት አካዉንት ባላቸዉ ሰዎች ሳይሆን ቤተሰብ ባላቸዉና በተከበሩ ሰዎች መሆኑ እንዳሳዘናት ተናግራለች።

> *"አንዳንድ ግዜ በሚደርሱብኝ የጥላቻ መልዕክቶች እገረምና የመልዕክት ላኪዎቹን አካዉንት እመለከታለሁ። የዉሸት ስምና ፎቶዎች ያሉባቸዉ አካዉንቶች ይሆናሉ ብዬ ብገምትም የቤተሰባቸዉን ፎቶ የሚለጥፉና ትክክለኛ አካዉንቶች መሆናቸዉን ስረዳ አዘንኩ"*

የጥቃት ፈፃሚዎቹን ማንነት ለመመርመር ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ።

.

## 5.3.3 የጥቃቶቹ ቅንጅት

ጥቃቶቹ የተቀናጁ እንደሆኑ የተጠየቁት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በተወሰነ መጠን ቢያምኑም ይህን በመረጃ ሊደግፉ አልቻሉም። ለምሳሌ አንድ ጋዜጠኛ ይህን ብላለች፡

> *"የኢንተርኔት ላይ ጥቃትን የሚያስተባብሩና የሚያቀናጁ ቡድኖች አሉ ብዬ አስባለሁ። በተለይም በጦርነቱ ወቅት አንድን ብሔር የሚወክሉ ቡድኖች በተደጋጋሚ ጥቃት ያደርሱብኝ ነበር። ጥቃቶቹም ታስቦባቸዉ የሚፈፀሙ እንደነበረ ግልፅ ነዉ።"*

በተመሳሳይ በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰራ ድርጅት ላይ ያለች መሪ ጥቃቶቹ የተቀነባበሩ እንደሆኑ ታምናለች

> *"አንድ ቡድን ጥቃቱን ሲፈፅም ተመሳሳይ የሆኑ ቃላቶችን በመጠቀምና በተቀነባበረ መልኩ ይፈፀማል።"*

ቪዲዮዎቿን ከሌሎች ቪዲዮዎች ጋር በማቀናበር የዉሸት መረጃዎች የተለቀቁባት አንድ ቲክቶክ ተጠቃሚ ይህን ብላለች፡

> *"ከእነዚህ ጥቃቶች ጀርባ የሆነ ያህል ቅንጅቶች በርግጠኝነት አሉ። በቲክቶክ መተግበሪያ ላይ አንድን ቪዲዮ ከሌላ ቪዲዮ ጎን አድርገሽ መልቀቅ የምትችይበት ስቲች (stitch) የሚባል ዘዴ አለ። ጥቃት ፈፃሚዎች ይህንን ቀላል ዘዴ ከመጠቀም ይልቅ ቪዲዮዎችን አዉርደዉ፣ ቆርጠዉና ቀጥለዉ ይለቁታል ።ይህ በጣም የሚገርምና ምን ያህል ታስቦበት የሚካሄድ ድርጊት እንደሆነ ማሳያ ነው። በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የሚያቀነባብሩ የተወሰኑ ገፆችና ቡድኖች አሉ ብዬ አስባለሁ።"*

በኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ዉጪ ያለዉን የሴቶች ጥቃት የሚያባብሱ የቲክቶክ ፕራንክ ገፆች አሉ። ለምሳሌ አንድ ተሳታፊ *"የኢትዮጵያን ቲክቶክ ፕራንኮች፣ አጫጭር ቪዲዮዎች ወይም አጫጭር ጭዉዉቶች ብትመለከቺ አንዷት ሴት ስትመታ ወይም ወሲባዊ አስተያየቶች ሲሰጡባት ታያለሽ"* ብላለች። ተሳታፊዋ ጠቁመዉ ስላዘጉት አንድ የቲክቶክ ገፅም ይህን ብላለች፡

> *"የዝግጅቱ አቅራቢ መንገድ ላይ ሴቶችን እየተከተለ ከለኋላቸዉ ቪዲዮ ይቀርጻል ከዛ የፊታቸውን ፎቶ ጨምሮ አንስቶ በገፁ ላይ ይለጥፍ ነበር። ማዘጋት ያልቻለዉና ከ50.000 በላይ ተከታዮች ያሉት ሌላ አካዉንትም ተመሳሳይ ድርጊቶችን ይፈፅማል።"*

በሴቶች መብት ላይ የሚሰራ ድህረ ገፅ ያላት አንዷት ሴትም እንደዚህ አይነት ገፆች እንዳሉና አሳባቢ እንደሆኑ እንደሚከተለዉ ገልፃለች።

> *"ቲክቶክ ላይ ሴቶች ላይ ጥቃት መፈፀም አንደ አንድ የዝግጅት ይዘት ሆኖ ይቀርባል። በመንገድ ላይ ወንዶች ሴቶችን ሲያጠቁ ወይም ክብረ-ነክ የሆኑ ንግግሮችን ሲናገሩ ዝግጅቶቹ ያሳያሉ። ታዋቂ የሆኑ የቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችም ሴቶች ላይ ጥቃት ሲፈፅሙ በግልፅ ይታያል"*

በተረጋገጡ ማስረጃዎች እጥረት ምክንያት ሲ አይ አር በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በተቀናጀ መልኩ እንደሚፈፅሙ ማረጋገጥ አልቻለም። ቀጣይ ጥናት ጥቃት ፈጻሚዎቹ ላይና ያላቸው የቅንጅት ምልክቶች ላይ ያስፈልጋል።

## 5.4 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተፅዕኖ

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የስራ ህይወትን ማበለሸት፣ የስነልቦና ጉዳትና የቤተሰብ ህይወት ላይ ችግር እስከመፍጠር የደረሱ መጠነ ሰፊ ተፅዕኖዎች አሉት ። በዚህም ምክንያት ብዙ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በዚህ ፍራቻ ከኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ዉጪ ካሉ ህዝባዊ መድረኮች ላይ ራሳቸዉን ማግለላቸዉን አሳዉቀዋል።

### 5.4.1 በግል፣ በስራ እና በቤተሰብ ህይዎት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ

ከ78 በመቶ በላይ የሚሆኑት የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ስለደረሰባቸዉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሲያወሩ የጭንቀትና ፍርሃት ስሜት እንደሚሰማቸዉ ገልፀዋል። አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ፌስቡክ ላይ በደረሰባት ጥቃት ምክንያት አደጋን ተከትሎ የሚከሰት የአዕምሮ መታወክ (Post-Traumatic Stress Disorder) እንዳጋጠማት ገልፃለች ። ብዙ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ከደረሰባቸዉ ጥቃት በኋላ በመልካቸዉ ዙሪያ በራስ አለመተማመን እንዳጋጠማቸው ገልፀዋል። አንድ ጋዜጠኛ በደረሰባት የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ድብርት ዉስጥ ገብታ እንደነበርም በዚህ መልኩ ገልፃለች፡

> *"ሰዎች የምፅፈዉን ነገር እንኳን ሳያነቡ መጥፎ አስተያየቶችን ሲሰጡኝ ድብርት ዉስጥ ገብቼ ነበር። ጤናዬም ላይ ተፅዕኖ ነበር"*

ሌላ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ የደረሱባት ጥቃቶች. . .

> *"[…] የኢንተርኔት መድረኩ ፅንፍ የያዘ እንደሆነና ይህንን እንደ ግለሰብ ችዬ መቀጠል እችል ይሆን ብዬ ራሰን እንድጠይቅ አድርገኛል። ጥቃቶቹ እኔ ላይ ተፅዕኖ አልፈጠሩም ብል መዋሸት ነዉ የሚሆነዉ"*

ለአንዳንዶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በእዉነተኛዉ አለም ላይ የመንቀሳቀስ ነፃነታቸዉን ሲገድብ ይታያል፡

> *"እንደ ጋዜጠኛ ከቤታችን ራቅ ያለ ወይም ጭር ያለ ቦታ አንሄድም ምክንያቱም እስካሁን ባየነዉ መሰረት በቡድን ከበዉሽ ይደበድቡሽና ሌላ ቦታ ይወሰዉዱሻል"*

አንድ የቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪ አዲስ አበባ ዉስጥ ስትንቀሳቀስ ደህንነት እንደማይሰማት በዚህ መልኩ ገልፃለች፡

> *"ፈጣሪ ይመስገን የድርጅት መኪና አለኝ እንጂ ከተማ ዉስጥ በነፃነት መንቀሳቀስ አልችልም። ድንገተኛ ጉዳይ ሲኖርብኝ ወይም መኪና ጥገና ክፍል ስትገባ እንዳልታወቅ ፊቴን በማክስ በመነፅር ሸፍኜ ነዉ የምንቀሳቀሰዉ"*

አንድ የሰብአዊ መብት መርማሪ ለህይወቷ በመስጋት አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደማትሄድ ገልጻለች። ለአለቃዋም *"የጥቃት ኢላማ ልሆን ስለምችል መሄድ አልችልም"* እንዳለችዉ ገልፃለች። ከኢንተርኔት ዉጪ በእዉነተኛዉ አለም ላይ ያሉ የግልና የቤተሰብ ደህንነት ስጋቶች እንዳሉ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል፡

> *"በዚህ ምክንያት ብዙ ስቃይ ደርሶብኛል። ልጆቼ ለሁለት ቀን ትምህርት ቤት አልሄዱም ነበር ። ባለቤቴም ስራዉን አቁሞ ከእኔ ጋር በየፖሊስ ጣቢያዉ ሲንከራተት ነበር። እኔም ባለቤቴም ስራ በማቆማችን ምክንያት የኢኮኖሚ ጫናው ከባድ ነበር። ማህበራዊ ተፅዕኖዎቹም ከፍተኛ ነበሩ"*

በቤተሰባቸዉ ዙሪያ ያሉ የደህንነት ስጋት በብዙዎቹ ቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ዘንድ የተነሳ ቁልፍ ነጥብ ነዉ። በሴቶች መብት ላይ የሚሰራ የእርዳታ ድርጅት ዋና ሃላፊ የልጆቿን ፎቶ ከግል ፌስቡክ ገጿላይ በመዉሰድ እሷ ላይ ላነጣጠሩ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች መፈፀሚያነት ሲዉሉ እንደነበር ገልፃለች። በዚህም ምክንያት ፌስቡክን መጠቀም እንዳቆመች ገልፃለች። ቤተሰቦቻቸዉን ሊደርሱባቸው ስለሚችሉ በቴክኖሎጂ እገዛ ለሚደረጉ ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ስለማዘጋጀት አስፈላጊነት ብዙ ተሳታፊዎች አንስተዋል።

> *“የሚያስፈራኝ ነገር ጉዳዩ የሚያመጣዉን ችግር እያወቅኩኝ በዚህ መንገድ መቀጠሌ በቤተሰቤ ላይ የሚያመጣዉ ተፅዕኖ ነዉ። በእኔ ምክንያት እነሱ ዋጋ መክፈል የለባቸዉም። ይህ ከቤተሰብ ጋር ዉይይት ይፈልጋል”*

የብዙዎቹ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ቤተሰቦች በኢንተርኔት ላይ ባላቸው ስራና የተሟጋችነት እንቅስቃሴ ዙሪያ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል። የስራ፣ የግልና የቤተሰብ ደህንነት ስጋቶች በኢንተርኔት ላይ ያላቸውን እንቅስቃሴ እንዲያቆሙ ምክንያት እንደሆኑ አንዳንድ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። አንድ ጋዜጠኛ *“ስራዬ ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ሲጀምርና ሰዎች ስለልጆቼ አስተያየት መስጠት ሲጀምሩ መቀጠል ጥሩ እንዳልሆነ ገባኝ”* ብላለች ።

## 5.4.3 የሴቶች ድምፅ መታፈን

ቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉ ብዙ ሴቶች የደረሰባቸው ጥቃት ኢንተርኔት ላይ ዝምታን እንዲመርጡና እንቅስቃሴያቸውን እንዲቀንሱ እንዳስገደዳቸው ገልፀዋል ። ክለብሀውስ የተባለውን ማህበራዊ ሚዲያ መጠቀም ያቆመች አንድ ቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ሀሳቧን እንዲህ አጋርታለች *“ጥቃቶቹ የስነልቦና ፈተና ናቸው። እኛን ዝም ለማሰኘት የሚደረጉ ናቸው”* በተመሳሳይ አንድ ጋዜጠኛ ጥቃት አድራሾቹ ድምጿን እንድታጠፋ ለማድረግ አስበው እንደተሳካላቸው ተናግራለች፡

> *“የሁሉም ጥቃት ፈፃሚዎች ዓላማ እኔን ዝም ማሰኘት ነበር። ይህም ተሳክቶላቸዋል። እኔ በግሌ አልፈራም ነገር ግን ስለ ሴት ልጄና ቤተሰቦቼ ደህንነት ሳስብ ይህን ያህል መሰዋዕትነት የሚገባው ማህበረሰብ አለ ወይ ብዬ ራሴን እጠይቃለው ። ድምፄን ለማሰማትና ሀሳቤን ለመግለፅ ወደ ኃላ የማልል ሰው ነበርኩ ። ይህንን ማንነቴን ሰርቀውኛል። ይህም የሆነው ፈርቼ ሳይሆን ከዚህ በላይ መሰዋዕትነት መክፈል ተገቢ ነው ብዬ ስለማላስብ ነው ።”*

አንድ ጋዜጠኛ ባደረሱባት ጥቃቶች ምክንያት ሙያውን እንደተወች ስትገልፅ ሙያውን ለሚቀላቀሉት አዳዲስ ሴት ጋዜጠኛ ያላትን ስጋት ትገልፃለች። *“ለምሳሌ ታናሽ እህት ቢኖረኝና ጋዜጠኛ መሆን እንደምትፈልግ ብትነግረኝ ብሞት ያንን እንድታደርግ አልፈቅድላትም”* ብላለች።

ብዙ ተሳታፊዎች ራሳቸውን መቆጠብ እንዳለባቸው ተናግረዋል። ለምሳሌ አንድ ጋዜጠኛ ስለ አንዳንድ ጉዳዮች መለጠፍ እንዳቆመችና *‘feminist’* የሚለውን ፅሁፍ በደረሷት መጥፎ አስተያየቶች ምክንያት እንዳጠፋች ተናግራለች ። አንድ የኢንተርኔት ጦማሪ በኢንተርኔት ላይ ያለው የመነጋገሪያ መድረክ እየጠበበ እንደመጣና ፅንፍ እየያዘ እንደሆነ ተናግራለች። ለምሳሌ፡

*"ከአስር ዓመት በፊት ወጣት ሴት ስለመሆን፣ ውርጃና ስለ ሴቶች ስነተዋልዶ ጤና አንድ ፅሁፍ ፅፌ ነበር። የተለያዩ ሰዎች ባልተስማሙባቸው ነጥቦች ዙሪያ ሞግተውኝ ነበር። እኔ ለፃፍኩት ምላሽ የሚሆኑ ፅሁፎች ሁላ ተፅፈው ነበር። በዚህም ደስተኛ ነበርኩ ። ይህን ሁኔታ አሁን ብታመጣው ግን ከባድ ነው።"*

በቃለ መጠይቁ ላይ በብዛት ባይነሳም ተስፋ እንዳለ የሚያሳዩ ሀሳቦች ነበሩ ። አንድ ጋዜጠኛ በቅርቡ ከአንድ ቲክቶክ ተፅዕኖ ፈጣሪ ጋር ስለነበራት ንግግር እንደዚህ ብላለች፡

*"ከአንድ ቲክቶክን እንደ ስራ የምትሰራና ለሴቶች መብት ተሟጋች ከሆነች ሴት ጋር ተወያይቼ ነበር። በምትሰራው ቪዲዮ ላይ ጥላቻ መልሶች የሚጠበቁ እንደሆኑና ይህም የበለጠ በጉዳዩ ላይ እንድትገፋበት እንደሚያበረታታት ተናግራለች። "*

ሌላ የቃለ-መጠይቅ ተሳታፊም *"የሚደርሱብኝ ጥቃቶች የበለጠ እንድታገል አድርገውኛል። ሴቶችን ዝም እያሰኙ ነው። እኔም በማደርገው እንቅስቀሴ እበረታለሁ"* ብላለች። ይህን አይነት ሀሳብ ያጋሩት ግን ጥቂት ተሳታፊዎች ብቻ ነበሩ።

### 5.4.3 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች መለመድ

ከፖለቲካ ፣ ብሔር ወይም ሃይማኖት ጋር የተገናኙ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የተለመዱና እንደጥቃት ወይም ትንኮሳ እንደማይታዩ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች መግለፃቸው አንድ የጥናቱ ቁልፍ ግኝት ነው ። አንድ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊ ያነሳችውና ከሌሎች ተሳታፊዎች ድጋፍ ያገኘ ሀሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*"ሴቶችን በኢንተርኔት መሳደብ እንደ ጥፋት የማይታይበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው ። በተለይም በህብረተሰቡ ዘንድ ዕውቅና ያላቸው ሴቶች፣ በቴሌቪዥን ላይ ቃለ መጠይቅ የሰጡ ሴቶች ወይም አጠቃላይ ኢንትርኔት ላይ ንቁ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን በአደባባይ ይዘለፋሉ። ሴቶችን ለማሳፈር መሞከር እና ራሷን የቻለችና በራስ መተማመን ያላት ሴት እንዳትፈጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ጨምሯል።"*

በኢትዮጵያ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉ ሴቶች ጋር ውይይት ያደረገች አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ይህን ብላለች *"በውይይቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩ ሴቶች ፈልገው ማህበራዊ ሚዲያን እስከተጠቀሙ ድረስ አብረውት የሚመጡትን ጥቃቶች መቀበል አለብን ብለው ያምናሉ።"* ሌላ ጋዜጠኛ ደግሞ ሴቶችን በኢንተርኔት ላይ መሳደብና ማስፈራራት *"ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ የኢንተርኔት ላይ መግባቢያ መንገድ ሆኗል"* ብላለች።

ለአንዳንዶቹ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የተለመደ ከመሆኑ የተነሳ እንደጥቃት እንደማይቆጥሩት አጋርተዋል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምን እንደሆነ አለማወቅና የስራው አካል እንደሆነ አድርጐ ማሰብ ብዙ ሴቶች በቃለ መጠይቁ ላይ እንዳይሳተፉ ምክንያት ሆኗል። አንድ ተሳታፊ ይህንን ብላለች፡

*"በምንነጋገርበት ወቅት ጉዳዩን እንደ ጥቃት ሁላ አናየውም ። በጣም ብዙ ጊዜ ከመከሰቱ የተነሳ የተለመደና ምንም ጥፋት እንደሌለው አርገን ነው የምናየው።"*

### 5.4.4 ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ጥቃቶችና እስራቶች

ብዙ ሴቶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ደደረገ ጥቃት የስነ ልቦና ጉዳትና አካላዊ ጥቃት የመሳሰሉ ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ተፅዕኖች እንደፈጠሩባቸው ገልፀዋል ። አንዷት ጋዜጠኛ ከቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታዊ ጥቃት ስለደረሰባት ጓደኛዋ እንዲህ ተናግራለች፡

*"ቦሌ አካባቢ ያለ መዝናኛ ቤት ውስጥ እየተዝናናን ሳለ መፅዳጃ ቤት ሄደች። ከዚያም ተከትለዋት ሄደው አካላዊ ጥቃት ለማድረስ ሙከራ አደርጉ። ስትጮህ የምታቃቸው ጥበቃዎች መጥተው አስጣሏትና ጥቃት አድራሾቹን አባረሯቸው "*

ሲ.አይ.አር ኢንተርኔት ላይ ያለው ጥቃት ከኢንተርኔት ውጪ ላለው አካላዊ ጥቃት መነሻ ይሁን ወይም ሁለቱም አይነት ጉዳዮች የአንድ ጥቃት የተለያዩ መገለጫዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ ኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ በሚፈፀሙ ጥቃቶች መሀከል ያለው ግኑኝነት ግልፅ ነው። ለምሳሌ ሴቶች በኢንተርኔት ላይ የሚደርስባቸው የመታሰር ዛቻ በእውነተኛው ዓለም ላይ የስነልቦና ጫና ይፈጥራል ።

ቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉ ሴቶች በስራቸው ምክንያት የመታስር ስጋት እንዳለባቸው ገልፅዋል ። አንድ የፖለቲካ ጋዜጠኛ በአንድ ወቅት በደረሰባት የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የተሰማትን የፍርሀት ስሜት እንደሚከተለው ገልፃለች፡

*"በግል የስድብ እና የዛቻ መልዕክቶች ቢደርሱብኝም እንድታሰር መንግስትን የሚጠይቁት መልዕክቶች ከሁሉም አደገኛ ነበሩ። ይህን ያልኩበት ምክንያት መንግስት ብዙሃኑንና አንዳንድ አክቲቪስቶች ለማስደሰት በህዝብ ጥያቄ መሰረት እስር ስለሚያካሂድ ነበር። በዚህም ምክንያት ከአሁን አሁን ታሰርኩ የሚል ስጋት ነበረኝ "።*

ለውጦች እንደሚኖሩ ቃሎች ቢገቡም የአብይ አህመድ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኃላም የጋዜጠኛ እስር ቀጥሏል። ብዙ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ስለታሰሩ ጓደኞቻቸው፣ የስራ ባልደረቦቻቸው እና ታዋቂ ሰዎች ተናግረዋል። ለምሳሌ አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢ ይህን ብላለች፡

*". . . የኔቲዩብ ላይ የምትሰራ ጋዜጠኛ ትናንትና ተወስዳለች፤ ስትወሰድ የሚያሳይ ቪዲዮ ይህንን ይመስላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ይህን ይመስላል ። በዚህ ቪዲዮ ምክንያት ሁላችንም እንቅልፍ አጥተናል ። ይህ ሁሉ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የተለያዩ ባለስልጣናት ጋዜጠኞች እንደማይታሰሩና የተሻለ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ቃል ከገቡ በኃላ መሆኑ የበለጠ አሳዝኖናል ። አንዷት ሴት ጋዜጠኛ በግልፅ ስትሰደብና ስትዋረድ ማየታችን በጣም ያስደነገጠንና እራሳችንን በእሷ ውስጥ ያየንበት ሁኔታ ነው። ይህ ሁኔታ ያለብን ስጋት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነና በእሳት እንደተከበብን ማሳያ ነው "።*

አንድ ጋዜጠኛ ስለደረሰባት የእስር ማስፈራሪያዎች ስትናገር በዛው በእሷ ስራ ምክንያት ቤተሰቦቿ ስለመታሰራቸው ይህንን ብላለች፡

*"ሴት መሆንሽን በማሰብ 'ይህን ስራ አቁመሽ አርፈሽ ልጆችሽን የማታሳድጊ ከሆነ ቤተሰቦችሽ ላይ ጉዳት እናደርሳለን' የሚሉ ጥቃቶች ይደርሱኛል ። ...ቤተሰቦቻችንም ፈርተዋል ። ለምሳሌ ወንድሜ በፖለቲካ ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎ ባይኖረውም አስረውታል። ለዚህ ነው ቤተሰቦቼ ዙሪያ ስጋት አለብኝ የምለው።"*

የስራ ባልደረባዋን መታሰር ተከትሎ አንድ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ሀገር ለቃ የሄደችበትን ጊዜ እንዲህ አስታውሳዋለች፡

> *"ሊያስሩኝ ቤቴ መጥተው ካጡኝ በኃላ ቤተሰቦቼ ደውለው ቤት እንዳልመጣ ነገሩኝ። የተዘጋጀ የቱርክ ቪዛና አውሮፕላን ቲኬት ስለነበረኝ መብረር ከተከለከሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ በረራ ቀኔን ቀይሬ አስቀድሜ ተጓዝኩኝ። ጠቡ ከመንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን ከህዝብ ጋር እንደሆነ ሳስብ ልቤ ይሰበራል። በሀገሬ ጎዳናዎች ላይ በነፃነት መራመድ እንደማልችል ሳስብ ይከፋኛል። "*

ሲ.አይ.አር በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለእነዚህ ክስተቶች በራሱ መነሻ መሆኑን ወይም በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት እንደ አጠቃላይ በሴቶች ላይ ለሚደርሰው ጥቃት አንድ መገለጫ መሆኑን ማረጋገጥ አልቻለም ።

በኢትዮጵያ በጋዜጠኞች ላይ የሚደርሰውን አደጋ በሃገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ተንታኞች ብዙ አስተያየት ሰጥተዋል። የትግራይ ጦርነትና ከመንግስት ተቃራኒ የሆነ ሀሳቦችን ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን የሸፈኑ ጋዜጠኞች ዛቻ ደርሶባቸዋል ፣ ተጠቅተዋል፣ ተገለዋል ፣ከሀገር ተባረዋል እና ያለ ፍርድ ታስረዋል።[16] በዚህም ምክንያት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች *"በህዝብ ፍርድ"* ምክንያት እንዳይታሰሩ ስጋት እንዳላቸው ገልፀዋል ። አንዲት ጋዜጠኛ ስለአንድ ጥቃት ፈጻሚ ባል በፃፈችው ፅሁፍ ምክንያት በጥቃት አድራሹና በአንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች ስላደረሰባት የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቀጥሎም ኢፍትሀዊ በሆነ መንገድ ስለታሰረችበት ሁኔታ እንዲህ ብላለች፡

> *" ተከስሼ የእስር ማዘዣ ወጣብኝ ። ይህ በአብዛኛው የሚሆነው አንድ ግለሰብ በመጀመሪያ ዙር ጥሪ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ሲቀር ነው ። ሰኞ ከሰዓት በኃላ 10 ሰዓት ላይ የፍርድ ቤት መጥሪያው ከደረሰኝ በኃላ በቀጣዩ ቀን ካዛንቺስ አካባቢ ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ አመራሁ ። ስደርስ በራሴ መምጣቴ ጥሩ እንደሆነና እነሱ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ቢያመጡኝ ጥሩ እንደማይሆን ነገሩኝ ። ዜናውና በዜናው ዙሪያ ያሉ መልሶች የያዘው ጋዜጣ ኮፒ በእጄ ላይ ነበር ።መርማሪውም የተከሰስኩባቸው ክሶች የሚገልፅ 23 ገፅ ፅሁፍ አነበበልኝ ።"*

ጋዜጠኛዋ በጽሁፉ ላይ ስሙ የተነሳው ግለሰብ መልስ እንዲሰጥ እድል እንደተሰጠውና ፅሁፍም በምትሰራበት ሚዲያ ተገምግሞ እንደተለቀቀ ገልፃለች። በመጨረሻም በዋስ እንደተለቀቀች ተናግራለች በፅሁፉ ዙሪያ ኢንተርኔት ላይ የነበረው የህዝቡ ምላሽ ለመታሰሯ አስተዋፅኦ እንዳደረገና በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና የህዝቡ አመለካከት በህግ ማስከበር ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ጋዜተኛዋ ተናግራለች። እንደዚህ አይነት ታሪኮች ጋዜጠኞችን በማሰር ለምትታወቀው ኢትዮጵያ ጥሩ ስም አይሰጧትም ።

## 5.5 በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል የተቀመጡ ምክሮችና መፍትሄ ሀሳቦች

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈፀመውን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከል የሚያግዙ መፍትሄ ሀሳቦች እንዲላቸው ጠቅሰው ነበር ። ምላሻቸው እንደሚከተለው ነው ።

[16] Reporters Without Borders (2023) Available at: https://rsf.org/en/country/ethiopia [accessed 19 April 2022]

ትምህርት እና ስልጠና

- ስለሰብዓዊ መብት ማለትም ስለ ክብር፣ ርህራሄ፣ አንድነት እና ፆታን፣ ብሔርን እና ሃይማኖትን መሰረት ስላደረገ እኩልነት የግንዛቤ ማስጨበጥ ዘመቻን ማድረግ
- በትምህርት ቤቶችና የስራ ቦታዎች ላይ ስለ ሚዲያ አጠቃቀምና ዲጂታል ደህንነት ማስተማር
- ለሴት ጋዜጠኞች ስልጠና በመስጠትና ሴቶች ማህበራዊ ሚናቸውን እንዲወጡ በማበረታታት የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶችን የመቋቋም ችሎታቸውን ማዳበር

የህግ ማሻሻያ ትግበራዎች:

- በጥላቻ ንግግር ዙሪያ ያሉ ህጎች ግልፅኝነት በተሞላበት መልኩ እንዲተገበሩ ማድረግና ተግባራዊነታቸውን ማሻሻል
- ከኢንተርኔት ላይ ጥቃት ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች ለህግ አካላትና ለማህበራዊ ሚዲያ ድርጅቶች ለማጋራት እንዲመች መሰብሰብና መመዝገብ
- በኢንተርኔት ላይ ሆነም ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እውቅና የሚሰጡ አዳዲስ ህጎች ማርቀቅ

የማህበራዊ ሚዲያ ድርጅቶችን ማሳተፍ

- በመተግበሪያዎቹ ላይ ጥቃቶች ሲኖሩ ለመጠቆም የሚያግዙ ዘዴዎችን፣ የአጠቃቀም ፖሊሲውን እና ማህበረሰቡ በፖሊሲው ዙሪያ ያለውን አመለካከት ማሻሻል
- በሁሉም ቋንቋ ሊጻፉ የሚችሉ ጥላቻ ንግግሮችን ለመለየት የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (Artificial technology) ቴክኖሎጂ መጠቀም
- ማህበራዊ ሚዲያዎች በተደጋጋሚ የማህበራዊ ሚዲያውን ህግ የሚጥሱ ገፆችን እንዲያግዱ ፣ የአካባቢውን ቋንቋ የሚናገሩ ተቆጣጣሪዎችን እንዲቀጥሩ፣ ተጠያቂነትን ለማስፈንና የአጥፊዎችን ማንነት ለመለየት በማህበራዊ ሚዲያ ማንነትን መደበቅ አንዲከለክሉ ጫና ማድረግ ያስፈልጋል ።

እንዚህ ምክረ ሀሳቦች በኢትዮጵያና በአለም አቀፍ ደረጃ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል እንደሚጠቅሙ ከዚህ በፊት የተፃፉ ጥናቶችም ያሳያሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ የኢንተርኔት ጥቃት ላይ  ምርመራ የሚያደርግ አለም አቀፍ ድርጅት ማቋቋም [17] እና ተፅዕኖ ፈጣሪና ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ስለ ኢንተርኔት ላይ ጥቃት ተፅዕኖ ጠቃሚ መልዕክቶችን እንዲያስተላለፉ ማድረግ[18] እንደ ተጨማሪ ምክረ ሀሳብ በጥናቶቹ ላይ ተገልፀዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ከማህበራዊ ሚዲያ ድርጅቶች ጋር የአጠቃቀም መመሪያን

[17] Stremlau (23 March 2022) The Citizen, Tanzania. Available at: https://www.thecitizen.co.tz/tanzania/oped/why-we-need-an-international-body-to-rein-in-hate-speech-during-conflict-3757350

[18] Workneh (2019) African Journalism Studies, Available at: https://www.tandfonline.com/doi/full/10.1080/23743670.2020.1729832; Yilma talks of media literacy campaigns: Yilma (2021) Cambridge University Press, Available at: https://www.cambridge.org/core/journals/journal-of-african-law/article/abs/on-disinformation-elections-and-ethiopian-law/AD43AE2160E071FEF73EE8E4128F0B7A

በማሻሻል  በቅርበት መስራት እንዳለበትና በጉዳዩ ዙሪያ የወጡ ህጎችን በተሻለ መልኩ ለመተግበር የተቋማትን አቅም መገንባት  እንደሚገባው ጥናቶች ይገልፃሉ።[19]

ብዙዎቹ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል የሚደረገው ዘመቻ ፍሬ የሚያፈራው ስትራቴጂዎቹ ተገቢውን ድጋፍ ሲደረግላቸውና ለብዙሃኑ መድረስ ሲችሉ እንደሆነ ያምናሉ። ሀገሪቱ ውስጥ ብዙ ብሔሮችና ቋንቋዎች እንደመኖራቸውና ችግሩን የቋንቋ ብዝሃነት ባለው መልኩ ለመቅረፍ መሞከር ተገቢ ነው። በተጨማሪም ጥሩ የሆነና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ለችግሩ ስርወ-መሠረት የሆኑ ጉዳዮችን ለምሳሌ በፆታ ዙሪያ ያሉ የጅምላ አስተሳሰቦችና ፆታን መሠረት ያደረጉ አድሎዎችን መከላከል አስፈላጊ እንደሆነ በጥናት ላይ የተሳተፉ ሴቶች ገልፀዋል።

[19] Yilma (2021) Cambridge University Press, Available at: https://www.cambridge.org/core/journals/journal-of-african-law/article/abs/on-disinformation-elections-and-ethiopian-law/AD43AE2160E071FEF73EE8E4128F0B7A

# 6. መደምደሚያ

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አያጠራጥርም። ጥቃቶቹ በአይነት፣ አላማ እና ተፅዕኖ እንደሚለያዩ ግን ይህ ጥናት ያሳያል። ወንዶችም ሆነ ሴቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ማህበራዊ መከፋፈሎች (በብሔር፣ ሃይማኖትና ፖለቲካ አመለካከት) ምክንያት የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም የጥቃቶቹ ባህሪ ግን የተለያየ እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ያምናሉ።

በቃለ መጠይቆቹ ተሳታፊዎች መሠረት ወንዶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ባላቸው የፖለቲካ አመላካከትና ወገንተኝነት ሲሆን ሴቶች ላይ የሚደርሱት ጥቃቶች ግን ሴትን የሚያሳንሱና በመልካቸውና ማህበረሰብ ውስጥ ካላቸው ሚና የሚመነጩ ናቸው። ለምሳሌ አንድ ተሳታፊ እንደገለፀችው በህዝብ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸው ሴቶች በፀጉራቸው፣ በሰውነታቸው ክብደት፣ በትዳር ሁኔታቸው፣ በሚጠረጠሩበት ፍቅረኛ እና በልጆቻቸው ቁጥር ዙሪያ በኢንተርኔት ላይ መነጋገሪያ ሲሆኑ ይህ ግን ተመሳሳይ ቦታ ላይ በሚገኙ ወንዶች ላይ እንደማይታይ ገልፃለች። ይህም ሴቶች የሚደርስባቸው ጥቃት ተጨማሪ ፆታዊ ይዘት እንዳለውና ዘላቂና በእውነተኛ አለም ላይ ተፅዕኖዎች እንዳሉት ያሳያል።

ቃለ መጠይቁ ላይ የተሳተፉት ሴቶች እንደገለፁት ጥቃቶቹ በራሳቸዉ ወይም በጥቃት አድራሾቹ ብሔር ፣ ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም ሃይማኖት ዙሪያ ቢሆንም የጥቃቶቹ አይነት ግን ፆታዊ ይዘት ነበራቸው። በብሔር፣ በፖለቲካዊ አመለካከት፣ በሃይማኖትና በፆታዊ ጥቃት መካከል ያለዉን ግንኙነት የሚያጠኑ ጥናቶች ተሰርተዋል። ሆኖም ግን በነዚህ ግንኙነቶች ምክንያት ሴቶች ከወንዶች በላይ ጥቃት እንደሚደርስባቸዉ ለማወቅና በሴቶች ላይ ያለዉ ተጨማሪ ተፅዕኖ ለመረዳት ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ።

ሴቶች ኢንተርኔት ላይ ስድብ፣ ማስፈራሪያና ዛቻ የመሳሰሉ የጥቃት አይነቶች ከማስተናገዳቸዉ በተጨማሪ ስማቸዉ ይጠፋል አልፎም ሚስጥራዊ መረጃቸዉ በኢንተርኔት ላይ ይለቀቅባቸዋል። ፌስቡክ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚፈፀምበት ዋነኛ ማህበራዊ ሚዲያ ቢሆንም በግልና ህዝባዊ በሆኑ ሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይም ጥቃት እንደሚደርስባቸዉ ገልፀዋል። ይህም ችግሩ ማህበራዊ መሆኑን እንጂ የአንድ ማህበራዊ ሚዲያ ድክመት ብቻ እንዳልሆነ ያሳያል።

የጥቃቶቹ ክብደት እንደመለያየታቸዉ ተፅዕኗቸዉም የተለያየ ነዉ። በዚህ ጥናት ላይ በተሳተፉት ሴቶች ላይ የደረሰዉ በቴክኖሊጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የስራ ህይወትን በማበላሸትና የስነልቦና ቀዉስን በማስከተል የቤተሰብ ህይወት ላይ ተፅዕኖ እስከመፍጠር ድረስ ደርሷል። ብዙ ሴቶች የእስራት፣አስገድዶ መደፈርና የግድያ ዛቻዎች ደርሶባቸዋል። የደረሰባቸዉን አካላዊ ጥቃትና እስራቶችም ተናግረዋል። አንድ የጥናቱ ተሳታፊ እስር እንደደረሰባት ስትናገር ሌላ ተሳታፊ ደግሞ ከእስር ለማምለጥ ከሀገር እንደተሰደደች ተናግራለች ። ሲ.አይ.አር በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገዉ ጥቃት የአካላዊ ጥቃቶቹና እስራቶቹ ቀጥተኛ ምክንያት ወይስ የኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ዉጪ የሚፈፀሙት ሁለቱም ጥቃቶች የአንድ ጥቃት የተለያየ አይነት መገለጫ መሆናቸዉ ማረጋገጥ አልቻለም። አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ኢንተርኔት ላይ ባለ ጥቃትና ከኢንተርኔት ዉጪ ባለ ጥቃት መካከል ያለዉ ግንኙነት ግልፅ ነዉ። ለምሳሌ ኢንተርኔት ላይ ያሉ የእስር ዛቻዎች እዉነተኛዉ አለም ላይ የስነልቦና ጉዳቶች እንደሚያምጡ ይታወቃል።

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ምክንያት ድምፃቸዉን እንዳያሰሙ እንደተደረጉና ከኢንተርኔት ዉጪ ያለዉ ህይወታቸዉን እንዲገድቡ መገደዳቸዉን ገልፀዋል።

ግብረሰዶም የሚል ስያሜ/ፍረጃ እንደተሰጣቸዉ ገልጸዋል። ግብረሰዶማዊነት በኢትዮጵያ ዉስጥ ህገወጥና በእስራት ሊያስቀጣ ይችላል።

እንደ ቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች የጥቃት ፈፃሚዎቹ አላማ ሴቶቹን ማዋረድ፣ ስም ማጥፋትና ማስፈራራት ሲሆን 50 በመቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች ደግሞ ሴቶችን ዝም ለማሰኘት እንደሆነ ያምናሉ። ሁሉም የቃለመጠይቁ ተሳታፊ ሴቶች በአንድ ድምፅ፣ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የተለመዱና እንደጥፋት እንደማይታዩ ተናግረዋል።የጥናቱ ተሳታፊዎች ጥቃቶቹ የተቀናጁ መሆናቸዉን ማሳያ ማስረጃ ባያቀርቡም ቅንጅት ሊኖራቸዉ እንደሚችል ማህበራዊ ሚዲያ እንቅስቃሴዎችን በማጥናት መረዳት ይቻላል። በጉዳዩ ላይ ጥልቅና ተጨማሪ ጥናቶች እንደሚያስፈልጉም ማመላከቻ ነው።

ሲ.አይ.አር ዓውደ ፅሁፋዊ ትንተና ፣የተዛማጅ ፅሁፎች ምልከተና ቃለ መጠይቆች በማድረግ የሰብዓዊ መብት ተማጋቾች ላይ የሚፈፀሙት የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች የትኞቹ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንደሚደርሱና  የጥቃቶቹን አይነት ፣አላማና ተፅዕኖ ለማየት ሞክሯል። የኢንተርኔት ላይ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ከሃይማኖት፣ ከዘርና ከፖለቲካ አንፃር በማጥናት ሴቶች  በእነዚህ ማንነታቸው  ምክንያት ከወንዶች የበለጠ ጥቃት ይደርስባቸው እንደሆነ መመርመር አስፈላጊ እንደሆነ  ይህ ጥናት አመላክቷል።

በዚህ ምርምር እና በዚህ የምርመራ መደምደሚያ ላይ፣ ሲ.አይ.አር ከማህበራዊ ሚዲያ የተውጣጡ ይዘቶችን ሰፋ ያለ ትንታኔ በማድረግ ጥናቱን ያሰፋዋል። የቃለ ምልልሱ ትንተና በኢትዮጵያ ውስጥ በብሔር እና በሃይማኖት የጥላቻ ንግግር ላይ ከተደረጉ ጥናቶች ጋር ተዳምሮ ሰፊ የጥላቻ ንግግር ምድቦችን ያነጣጠረ የስብስብ እቅድ መሰረት ይሆናል። ይህም በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች የሚደረጉበት በታና የጥቃቶቹ አይነት እንደሚለያዩ ለማሳየት ያግዛል።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን በዘላቂነት ለመከላከል የሚነደፉ ስትራቴጂዎች የችግሩን ስር መሰረት ለመቅረፍ ያለሙ መሆን እንዳለባቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ይህም በሴቶች ዙሪያ ያሉ የጅምላ አስተሳሰቦችንና የፆታ መገለልን በመቀነስ ሴቶች በኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ባሉ ሚዲያዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ መጨመርን ያካትታል። ይህም ሴቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ሚና እንዲጫወቱ ያበረታታል።

Centre for Information Resilience